# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 273 ሰኔ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ካላቸው የእስያ ሀገራት ምን ትቀስማለች?

**መዓዛ ማሞ**

ሀገራት እንደሚከተሉት ፖሊሲ እና ስተራቴጂ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃቸው ይለያያል፡፡ የሀገራት የማያቋርጥ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ሀገራቱ በኢኮኖሚ ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ ለዜጎች ምቹ ሀገር ከመፍጠር አኳያ ትልቅ ድርሻ እንዳለው የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

ከእስያ ሀገራት መካከል በተለይ አራት ሀገራት ተከታታይ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ "እስያ ታይገርስ" የሚል ስያሜ በማግኘት ይታወቃሉ፡፡ ሀገራቱ ሆንግ ኮንግ፣ ሲንጋፖር (ቻይና) ፤ታይዋን እና ደቡብ ኮሪያ ናቸው፡፡

ሀገራቱ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የጀመሩት እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ1960 ጀምሮ ሲሆን ከዚያ በፊት ኋላቀርና ኢኮኖሚያቸውም እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ታሪካቸው ያስረዳል፡፡

እነዚህ ሀገራት በፖሊሲያቸው ያላቸውን እና የሌላቸውን ሀብት በመለየት የወጪ ንግድን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ አብዮት አካሂደዋል፡፡ የትምህርት ጥራት ላይ እንዲሁም ለቴክኖሎጂ እድገት ትኩረት ሰጥተው ሠርተዋል፡፡ በዚህም የማያቋርጥ እድገት እያስመዘገቡ በመቀጠል እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በማደግ ላሉ ሀገራት ጥሩ አርአያ መሆን መቻላቸውን ብዙዎች ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ እና ተከታታይ ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር እና የቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን መምህር ለገሰ ቁጥሬ (ዶ/ር ) በጉዳዩ ላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራቱ


**ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# የትምህርት ጥራት ወዴት አለ?

**ዘላለም ግዛው**

ጥራትን ከማስጠበቅ ይልቅ ብዛት ላይ ማተኮሩና ፖለቲካው በትምህርት ሥርዓቱ ጣልቃ መግባትና ለመምህራን ተገቢ ትኩረት አለመሰጠቱ ለትምህርት ጥራት መውደቅ ምክንያት ሆኗል ሲሉ መምህራን ይወቅሳሉ፡፡

በዘርፉ የደረሰውን ስብራት ለመጠገን መንግሥት የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ርምጃዎች እየወሰደ ሲሆን፤ የመውጫ ፈተና፣ የሥርዓት ትምህርት ክለሳና መምህራንን በመፈተን የቀጠለው ተግባር በአብነት ይጠቀሳል፡፡


መመህራን ግን ለትምህርት ጥራት መሻሻል እየተወሰዱ የሚገኙት ርምጃዎች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ ወሳኝ የሆነው የመምህራን ብቃት፣ ለስራ ያላቸው ቁርጠኝነት እና በሥራ ላይ ያላቸውን ርካታ ማስጠበቅ ተዘንግቷል ይላሉ፡፡

በዘርፉ ጥናትና ምርምር የሠሩት አማኑኤል ኤሮሞ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የትምህርት ጥራት የሚሻሻለው በመማር ማስተማር፣ የመምህራንን ብቃት በማሳደግ፣ መምህራን ለመማር ማስተማር ያላቸውን ቁርጠኝነትና


**የትምህርት ጥራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት ለቀጣናው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ ሚና ይኖረዋል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት በቀጣናው ዘላቂ ሠላምን በማረጋገጥ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰፕላይ ቸን ማኔጅመንት ምሁር ማትዮስ ህንሰርሙ ( አሶሸት ፕሮፌሰር ) ገለጹ።

ማትዮስ (አሶሸት ፕሮፌሰር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት በቀጣናው ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ከማስቻሉም በላይ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብም ተባብሮ ማደግ ያስችላል፡፡

ኢትዮጵያ ባሕር በር ሳይኖራት የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ቢሆንም ከዚህ የበለጠ ለማደግ ባሕር በር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፤ የባህር በር ለኢትዮጵያ የህልውናና አብሮ የማደግ ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ባህር በር አጠቃቀም ሕጎች መሠረት ማንኛውም ሀገር ባሕር በር የመጠቀም መብት የሚከለክል


**የኢትዮጵያ ባሕር በር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**














ዜና



ኤፍሬም ገብረሃና (ዶ/ር)

# በኢትዮጵያ ውስብስብ የአጥነት ህክምናዎችን መስጠት የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ውስብስብ የሚባሉ የአጥንት ህክምናዎችን መስጠት የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል ሲል የኢትዮጵያ የአጥንትና የአደጋዎች ሕክምና ስፔሻሊስቶች ማህበር ገለጸ።

የአጥንትና የአደጋዎች ሕክምና ስፔሻሊስቶች ማህበር ያዘጋጀው 17ኛው ሳይንሳዊ ጉባዔና ዐውደ ርዕይ ሰሞኑን ሲካሄድ የማህበሩን ፕሬዚዳንት ተወካይና የአጥነት ሕክምና ስፔሻሊስት ኤፍሬም ገብረሃና (ዶ/ር)፤ የአጥንት ህክምና የተለያዩ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ስለሚፈልግ ከዚህ በፊት ታካሚዎች ከሀገር ውጭ ሄደው ህክምናውን ይከታተሉ እንደነበር አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ለተለያዩ የአጥንት ህክምናዎች የሚያገለግሉ ዘመናዊ መሣሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ፤ በኢትዮጵያ ውስብስብ የሚባሉ የአጥንት ህክምናዎችን በስፋት መስጠት ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር ኤፍሬም እንደገለጹት፤ በተለይም የሰውነት መገጣጠሚያ ቅየራ፣ በካሜራ እገዛ የሚደረግ ቀዶ ህክምናና ከአጥንት ጋር የተያያዙ የጀርባ ቀዶ ህክምናዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች እየተሰጡ ይገኛል።

አሁን ላይ ቴክኖሎጂውም ሆነ ባለሙያዎች በሀገር ውስጥ በመኖራቸው ሰፊ ርቀት መጓዝና ተጨማሪ ወጪ ማውጣት አያስፈልግም፤ ማህበሩም ይህን የሀገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት ያበረታታል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የአጥንት ህክምና ዘርፍ ባለፉት 10 ዓመታት በተሠሩ ሥራዎች የተሻለ ለውጥ መታየቱን ጠቁመው፤ ከዚህ በፊት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ሲሰጥ የነበረ የአጥንት ህክምና ትምህርት አሁን በተለያዩ 11 ቦታዎች እየተሰጠ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

እየተስፋፋ በመጣው የመኪና አደጋና ባለፉት ጊዜያት ባጋጠሙ ጦርነቶች ምክንያት በኢትዮጵያ የአጥንት ህክምና የሚፈልጉ ታካሚዎች ቁጥር መጨመሩን የተናገሩት ዶክተር ኤፍሬም፤ የአጥንት ስብራትና መመርቀዝ ችግር በስፋት ለማከም ማህበሩ ትኩረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

የጉባዔው ዓላማ ከአጥንት ስብራትና መመርቀዝ ጋር ተያይዞ ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በሀገር ውስጥ ካለው ጋር ለማነጻጸር ፤ ለባለሙያዎች ሥልጠና ለመስጠትና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ያለመ መሆኑን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ማህበሩ በሰራው ጥናት መሠረት በባህላዊ መንገድ የአጥንት ህክምና ለማድረግ በሚደረግ ጥረት በርካታ ህጻናትና አዋቂዎች ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህ ረገድ እንደሀገር ማህበሩ ጥናት ማድረጉን ጠቅሰው፤ ችግሩን ለመፍታት በስፋት ችግሩ የሚገጥማቸው ህጻናት እንደመሆናቸው ለመምህራንም አገልግሎታቸውን እንዲያጠናክሩ ሥልጠና እየተሰጠ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በቀጣይ የአጥንት ህክምናን ለማሳደግ የህክምና መሣሪያዎች ከውጭ ሀገራት በሚገቡበት ወቅት ከጉምሩክ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ እንግልቶችን ማስቀረት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በጉባኤው ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለተገኙ የአጥንት ህክምና በለሙያዎችና ተማሪዎች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ በዐውደ ርዕዩ የተለያዩ የአጥንት ህክምና መሣሪያዎች ለእይታ ቀርበዋል።

# ለመቄዶኒያ 40 ሚሊዮን ብር የሚገመት
## መኖሪያ ቤት በስጦታ ተበረከተለት

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- መጋቢ ጥበባት ሰለሞን ታደሰና ወይዘሮ አበባየሁ ታደሰ ከታላቅ እህታቸው ወይዘሮ አዲስ ታደሰ በውርስ ያገኙትን መኖሪያ ቤት ለመቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል በስጦታ አበረከቱ።

የማዕከሉ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ (የክብር (ዶ/ር) የመኖሪያ ቤት ስጦታውን ትናንት በማዕከሉ ተረክበዋል።

ድጋፉን ያስረከቡትና ነዋሪነታቸው በሀገረ አሜሪካ የሆነው መጋቢ ጥበባት ሰለሞን ታደሰ መኖሪያ ቤቱን ከታላቅ እህታቸው ወይዘሮ አዲስ ታደሰ በህጋዊ መንገድ መውረሳቸውን አስታውቀዋል።

መኖሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ባልቻ ሆስፒታል ጀርባ በ158 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሲሆን፤ አሁን ባለው ዋጋ 40 ሚሊዮን ብር የሚገመት ነው ብለዋል።

ቤቱን በማስረከባቸው መደሰታቸውን ገልጸው፤ በቀጣይም በሚኖሩበት ሀገር ሌሎች ሰዎችን በማስተበበር ለመቄዶንያ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

ወይዘሮ አበባየሁ ታደሰ በበኩላቸው ከእህታቸው በውርስ ያገኙትን ቤት ለመቄዶንያ ያስረከቡት ማዕከሉ በሚፈልገው ሁኔታ እንዲገለገልበት መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይም አቅማቸው በሚፈቅደው ልክ ድጋፍ እንደሚያደርጉ አመላክተዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የማዕከሉ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ (የክብር (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የመኖሪያ ቤት ስጦታው የመረዳዳት ባህልን የሚያጎለበት እና ከቤተሰብና ከተለያዩ ሰዎች ወርሰው በክርክር ላይ ለሚገኙ ሰዎች ትልቅ አርዓያ የሚሆን በጎ ተግባር ነው።

ሌሎች ሰዎችም ይህንን አርዓያነት ያለው ተግባር በመከተል የወረሱትን፣ የራሳቸውን፣ በስጦታና በተለያየ መንገድ ያገኙትን ገንዘብና ንብረት ለመቄዶንያ ቢሰጡ ዋጋው ዘላለማዊና ሰማያዊ መሆኑን ተናግረዋል።

ማዕከሉ ቋሚ ገቢ፣ የውጭ ሀገር ፈንድና ንግድ የሌለው በመሆኑ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች ድጋፍ እንዲያደርጉ አስገንዝበዋል።

ማዕከሉ በአሁኑ ጊዜ 27 ቅርንጫፍና ሰባት ሺህ ተገልጋዮች እንዳለው ገልጸው፤ በቀጣይ ቅርጫፉን 130 በማድረስ ተገልጋዮችን ወደ 20 ሺህ ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

መጋቢ ጥበባት ሰለሞን ታደሰን እና ወይዘሮ አለማየሁ ታደሰን ላበረከቱላቸው ስጦታ አመስግነው ሌሎች ሰዎችም ከዚህ ትምህርት በመውሰድ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።



# ወለጋ የልማት ተምሳሌት እየሆነች ነው

## - በክልሉ ዘንድሮ ለአረንጓዴ ዐሻራ አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ዝግጁ ሆኗል

**በኃይሉ አበራ**

ነቀምት፡- ወለጋ የልማት ተምሳሌት ሆናለች ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ተናገሩ። በክልሉ ለዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ዝግጁ መሆኑ ተጠቁሟል።

በምስራቅ ወለጋ ዞን ጎቦሰዮ ወረዳ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሰሞኑን ጉብኝት ተደርጓል።

በጉብኝቱ ወቅት የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለብዙኃን መገናኛ እንደገለፁት፤ በወለጋ በተለይም በምስራቅ ወለጋ የተጎበኙ የተለያዩ የግብርና ልማቶች ወለጋ የልማት ተምሳሌት መሆኗን አመላካች ናቸው።

በጎቦሰዮ ወረዳ የአፈር ማዳበሪያ በመጠቀም በክላስተር የሚለማ የበቆሎ የእርሻ ዝግጅት ሥራ መጎብኘቱን ጠቁመው፤ በወረዳው ከዚህ በፊት ብዙም ያልተለመደ እና ባለፉት አራት ዓመታት የተከናወነ የአቮካዶ ምርት ውጤታማ መሆኑን ተናግረዋል።

በወለጋ አራቱም ዞኖች የሚደረጉት የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች ምርታማ መሆኑን ጠቁመዋል። ቀደም ሲል በወለጋ ምንም የልማት እንቅስቃሴ እንደሌለ አድርጎ የማየት ሁኔታም የተሳሳተ መሆኑን በተጨባጭ የታየበት መሆኑንም ገልፀዋል።

ለምግብነት የሚውሉና ለአየር ንብረት ለውጥ እገዛ የሚያደርጉ ችግኞች መዘጋጀታቸውን አንስተው፤ በተለይም ከዚህ በፊት በአካባቢው ያልተለመደው የሞሪንጋ ምርት እንዲለመድ የሚያግዙ ችግኝ ዝግጅት በስፋት እየተሠራበት መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ አመላክተዋል።

ከነቀምት ከተማ 52 ኪሎ ሜትር ላይ የምትገኘው ጉቶ ጊዳ ወረዳ ቀደም ሲል የሰላም ችግር ውስጥ ቆይታለች ያሉት ኃላፊው፤ አሁን ላይ ወረዳዋ ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚታይባት እና የልማት ወረዳ መሆኗን የወረዳው አስተዳደር አቶ ተመስገን ገቢሶ አስረድተዋል። በወረዳዋ 96 ያህል ባለሀብቶች በግብርና ሥራ ላይ እየሠሩ ይገኛል ብለዋል።

በዘንድሮው ዓመት 1 ሺህ 664 ሄክታር በስንዴ ልማት ለመሸፈን ከታቀደው 112 በመቶ ተግባራዊ መደረጉን አቶ ተመስገን ተናግረዋል።

የክላስተር ሥራዎችን በተመለከተም በወረዳው በዚህ ዓመት ከ58 ሺህ ሄክታር በላይ ለማረስ ታቅዶ በክላስተር እና በግል በመዝራት በመጠናቀቅ ላይ ነው ብለዋል።

በወረዳው ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል እና የመሬት ለምነትን ለማሳደግ በቂ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና የአፈር ሕክምና አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል። በወረዳው በዋናነት የበቆሎ ምርት የሚመረት ሲሆን የቅባት እህሎች፣ ለውዝ፣ አኩሪ አተር እየተመረተ መሆኑን አንስተዋል።

የግብርና ቢሮ በክልሉ ለዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ዝግጁ መሆኑንም አሳውቋል። በተለይም ለምግብነት የሚውሉ በእቅድ ከተያዘው 500 ሚሊዮን ችግኝ 490 ሚሊዮን ያህሉ ዝግጁ መሆናቸው ተመላክቷል።

በአረንጓዴ ዐሻራው ከሚተከሉትም 11 በመቶ ለምግብነት የሚውሉ ናቸው። በዘንድሮ ዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ላይ ለመትከል ታቅዷል። ከ680 ሺህ ሄክታር በላይ የት ቦታ ላይ ምን መትከል እንደሚገባው መለየታቸው ተጠቁሟል።

በተጨማሪ በምስራቅ ወለጋ ሲቡስሬ ወረዳ የአረንጓዴ ዐሻራ ዝግጅት ተጎብኝቷል።



አቶ ኡስማን ሱሩር

# በክልሉ ከበጋ መስኖ ልማት 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኘ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በበጋ መስኖ ልማት 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት መገኘቱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በበጋ መስኖ ልማት ሥራው ከ33 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል እንደተፈጠረላቸው ተመላክቷል።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርናና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪ እና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ገበያው የሚፈልገውን እና ክልሉ ባለው የመሬትና የውሃ አቅም ልክ የበጋ መስኖ ልማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ ቆይቷል።

በበጋ መስኖ ልማት 147 ሺህ ሄክታር መሬት በማልማት 33 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ፤ 147 ሺህ 500 ሄክታር መሬትን በማልማት 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት መገኘቱን አስታውቀዋል።

በበጋ መስኖ ልማት ከለማው 147 ሺህ 500 ሄክታር መሬት ውስጥ ሁለት ሺህ 600 ሄክታር መሬትን በበጋ ስንዴ በማልማት ከ100 ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

ቀሪውን መሬት ገበያው የሚፈልገውን ቃሪያ፣ ሽንኩርት፣ ጥቅልና ሀበሻ ጎመን፣ ቲማቲም እና ሌሎች የአትክልት አይነቶችን በማልማት የአትክልት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ በግብርና ምርቶች ላይ የነበረውን የዋጋ ንረት መቀነስ እና ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር እንደተቻለ ጠቅሰዋል።

በክልሉ ከጥቅምት ጀምሮ እስከ ታህሳስ 2016 ዓ.ም ድረስ ቲማቲም በኪሎ በአማካኝ ከ80 ብር እስከ 100 ብር፤ ሽንኩርት ከ180 እስከ 200 ብር ሲሸጥ እንደነበር አውስተው፤ ከጥር ወር ጀምሮ በበጋ መስኖ የለሙት አትክልቶች ለገበያ ሲደርሱ ያለማንም ተቆጣጣሪ ቲማቲምን በኪሎ ከ10 እስከ 20 ብር ሽንኩርትን ከ35 እስከ 55 ብር ለገበያ ማቅረብ እንደተቻለ አስረድተዋል።

በበጋ መስኖ የተመረቱት አትክልቶች የክልሉን ገበያ ጨምሮ፣ የአጎራባች ክልሎችንና የማዕከል ገበያዎችን ለማረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ገልጸው፤ በቀጣይም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ማዕከል ድረስ ያለውን የአትክልት ገበያ ለማረጋጋት በትኩረት እንደሚሠራ አመላክተዋል።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከዚህ በፊት ያልተለመዱ እንደ ዝኩኒ፣ ሃብሀብ እና ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ አይነቶችን ማምረትና የክልሉን የሥራ ባህል መቀየር ተችሏል ብለዋል።

የበጋ መስኖ ሥራ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአካባቢውን ማህበረሰብ ኑሮ ለማሻሻል ከአበረከተው አስተዋጽኦ ባለፈ ከ33 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ማድረጉን አስረድተዋል።

# 76 አዳዲስ የገጠር ከተሞች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆነዋል



አቶ መላኩ ታዬ

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት 10 ወራት በኢትዮጵያ 76 አዳዲስ የገጠር ከተሞችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ። የተቋሙ የአገልግሎት ታሪፍ ወጪን መሠረት ያደረገ አለመሆኑ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት እንቅፋት መፍጠሩ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ባለፉት አስር ወራት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ተደራሽነትን ለማስፋት የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በዚህም 76 አዳዲስ የገጠር ከተሞችንና መንደሮችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

አቶ መላኩ ባለፉት አስር ወራት ከ328 ሺህ በላይ አዲስ ደንበኞች ኃይል እንዲያገኙ መደረጉን ጠቁመው፤ ከነዚህም ውስጥ 31 ሺዎቹ በሚያዚያ ወር አገልግሎቱን ያገኙ መሆናቸውን አብራርተዋል።

የተቋሙ የአገልግሎት ታሪፍ ወጪን መሠረት ያደረገ አለመሆኑ፣ ሂሳባቸው የማይከፍሉ መንግሥታዊ ተቋማት መኖራቸው፣ የፀጥታ ችግርና የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያዎች አቅም ውስንነት የተቋሙ አፈጻጸም እንዳያድግ ምክንያት መሆናቸውን አንስተዋል።

በተለይም የሀገሪቷ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ካለው የዋጋ ግሽበት አንጻር ወጪን የማይሸፍን መሆኑ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠትና ገጠራማ የሀገሪቷ ክፍሎች ላይ በስፋት የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ለማድረግ እክል መፍጠሩን አመላክተዋል።

በቀጣይ የታሪፍ ማሻሻያ ተግባራዊ ለማድረግ ጥናት ተጠናቆ ወደሚመለከው አካል መቅረቡን ገልጸዋል።

# አስተዳደሩ ለአረንጓዴ ዐሻራ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ችግኞች አዘጋጀ

ኤፍሬም አንዳርጋቸው

ማያ ሲቲ፡- ለዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ከ5 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል መዘጋጀቱን በኦሮሚያ ክልል የማያ ከተማ አስተዳደር ገለጸ።

የማያ ከተማ ከንቲባ ዶክተር ኢፍረሃ ወዘር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ እንደገለጹት፤ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለምስራቁ የሀገራችን ክፍል በተለይም ለከተማዋ ያለውን ከፍተኛ ጥቅም በመረዳት በየዓመቱ በሚሊዮች የሚቆጠር ችግኞችን እየተተከሉ፣ ክትትልና እና እንክብካቤ እየተደረገባቸው ይገኛል።

ለአብነትም በባለፈው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ወቅት የከተማው አስተዳደር እና ማህበረሰብ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከ4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ችግኝ መተከሉን አውስተው፤ ከተከላ በኋላ በተሠራው የመንከባከብ እና የመጠበቅ ሥራ ከ82 በመቶ በላይ ችግኞች መጸደቃቸውን ተናግረዋል።

በዘንድሮ ዓመትም ወጣቶችን እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ባሳተፈ መልኩ የአፈርና ጥበቃ ሥራ እንዲሁም የችግኝ መትከያ ቦታ የማዘጋጀት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት ከንቲባዋ፤ በዚህም ከ5 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል የዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል። በተለይም ህብረተሰቡ ችግኞችን ለመትከል ካለው ተነሳሽነት አንፃር ችግኞች እንዳያንሱ እና ተጨማሪ ችግኞችን ለመትከል እንዲቻል ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ተጨማሪ ችግኞችን እያዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመቀናጀት የሚሠራቸው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የሐረማያ ሐይቅ እንዲመለስ ማድረጉን ጠቅሰው፤ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ደግሞ የሐይቁ ውሃ ቀጣይነት እንዲኖረው፣ ጥልቀቱ እንዲጨምር፣ ህብረተሰቡ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረገ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።



ዶክተር ኢፍረሃ ወዘር

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ የከተማው አስተዳደር ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በቅንጅት መሥራቱ ችግኞች በዘፈቀደ የትኛውም ቦታ ላይ እንዳይተከሉ እና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንክብካቤ እና ጥበቃ እንዲደረግላቸው አስችሏል። በተጨማሪም ችግኞች የት ቦታ እንደተተከሉ ለማወቅ እና መጽደቅ አለመጽደቃቸውን ቦታው ድረስ ሄዶ ለማየት፣ ለምርምርና ለቀጣይ ስትራቴጂ ነደፋ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ፡፡

የማያ ከተማ በ3 ሺህ 710 ሄክታር መሬት ላይ አወዳይ፣ አዲ ኢሌ እና ሐረማያ ክፍለ ከተሞች ላይ በ12 ቀበሌዎች ተደራጅቶ የተመሠረተ ከተማ ነው።

# የትምህርት ጥራት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሥራ ርካታን በማሳደግ ነው። ኑሮውን ለማሸነፍ ላይ ታች የሚለውን መምህር በተማሪ ላይ ለውጥ ያመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም።

ፈተና ስብራቱን አያስተካክልም፣ የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ ከተፈለገ የመምህሩን ደመወዝ ማስተካከል ያስፈልጋል። መምህሩ ብቃት ቢኖረውም ቁርጠኛ አይደለም፣ ቁርጠኝነት አለው ቢባልም የሥራ ፍላጎት ያንሰዋል ይላሉ።

የትምህርት ጥራት ስብራት መኖሩ የታወቀው 1999 ዓ.ም ነው። በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የትምህርት ቤት ማሻሻል፣ የመምህራን ልማት፣ የትምህርትና ቴክኖሎጂን ትስስር ጨምሮ ስድስት መርሃ ግብሮች ተነድፈው ቢተገበሩም፣ በተለያየ ደረጃ የተደረጉ የጥናትና ምርምር ውጤቶች መርሃ ግብሮቹ ውጤታማ አለመሆናቸውን ያሳያሉ ነው የሚሉት።

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህሩ ዘላለም ወዳጆ፤ ለኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት መውደቅ መዘዞቹና የመፍትሄ ርምጃዎችም የተለያዩ መሆናቸውን ያነሳሉ።

መምህር ዘላለም፤ መንግሥት ለመምህራን ተገቢ ትኩረት አለመስጠቱ፣ መምህራን ተገቢ ጥቅምና እድገት አለማግኘታቸው ይጠቁማሉ።

መምህራን ወደ ማስተማር ሥራ ሲገቡ በቂ ዝግጅት አለማድረጋቸውም ለውድቀቱ ችግር ሆኖ ይነሳል የሚሉት መምህሩ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አሠልጣኞች የተነሳሽነት ማነስ መኖሩና ተማሪዎቹ በአግባቡ ሳይበቁ በሶስት ዓመታት ተመርቀው መውጣታቸው ችግሩን እንዳባባሰው ያነሳሉ።

ሥርዓተ ትምህርት ተለዋዋጭና እየተሻሻለ የሚሄድ ቢሆንም፤ ጉድለቱ ሳይፈተሽ መለዋወጡ በከፍተኛ ትምህርት ላይ ለተፈጠረው የጥራት ጉድለት አንዱ ምክንያት መሆኑንም ያመለክታሉ።

አማኑኤል (ዶ/ር) እንደሚሉትም፤ ለላቀ ውጤት መገኘት የመማር ማስተማር ሥርዓት ካልተስተካከለ የተማሪ ውጤት ሊስተካከል አይችልም። መንግሥት ስታንዳርዱን ለማረጋገጥ ፈተና መስጠት ቢችልም ፈተና የትምህርት ጥራትን አያመጣም።

የትምህርት አመራሩ ሙሉ ጊዜውን በትምህርት ቤት በማድረግ መምህርና ተማሪውን መደገፍና መከታተልም አለበት። ነገር ግን በኢትዮጵያ ሁኔታ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ውጤቶች እንደሚያሳዩት የአብዛኞቹ ርእሰ መምህራን የምልመላ ሂደት ችግር አለበት፤ ከተመለመሉ በኋላም አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሳይሆን በፖለቲካ ሥራ ነው ይላሉ።

ላለፉት 20 እና 30 ዓመታት ትምህርት ፖለቲካ መሆኑን የሚገልጹት መምህር ዘላለም፤ አንዳንድ መምህራን ፖለቲካውን ተጠግተው ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት የትምህርት ሥርዓቱን ጎድቶታል ይላሉ።

የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው የትምህርት ጥራት የሚመጣው በአንድ ሥርዓት ውስጥ ተጠያቂነት ሲኖር ነው የሚሉት አማኑኤል (ዶ/ር)፤ በኢትዮጵያ የትምህርት አዋጅ አልታወጀም፣ የትምህርት ሕግ ባለመኖሩም ተጠያቂነት አልሰፈነም። ባለፈው ዓመት ከአንድ ሺ በላይ ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ አላሳለፉም፣ በቀጣዩም ተመሳሳይ ውጤት ተደግሟል ለውድቀቱ ግን ተጠያቂም ኃላፊነት የወሰደም የለም ሲሉ ይወቅሳሉ።

ለውድቀት መንስኤ የነበሩ ምክንያቶች ተለይተው ስትራቴጂዎች ተቀይሰው ክፍተቱን ለመሙላት ባለመሠራቱ ተመሳሳይ ውጤት ተደግሟል፣ አሁንም ተመሳሳይ ውጤት ሊደገም ይችላል የሚል የአማኑኤል (ዶ/ር) ስጋት አላቸው።

የትምህርት ሕግ አለመኖሩና ተጠያቂነትም ባለመስፈኑ የኢትዮጵያ የትምህርት ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሽቆልቆሉን ቀጥሏል ባይ ናቸው አማኑኤል (ዶ/ር)።

መምህራን መፈተናቸው ድክመትና ጥንካሬያቸውን እንዲያዩበት ያግዛቸዋል የሚሉት መምህር ዘለላም፤ የሚያስተምሩትን ትምህርት ተፈትነው የወደቁ ወይም ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ መምህራን ራሳቸውን እንዲፈትሹ፣ ለማሻሻል እንዲነሳሱ ይጠቅማቸዋል ባይ ናቸው።

መምህራን መፈተናቸው ጥቅም አለው፤ ነገር ግን ፈተናው መስፈርት ሊኖረው ይገባል። ለዓላማው በትክክል የተዘጋጀና ሙያዊ ብቃትን ለመገምገም ከሆነ ያንን ያማከለ መሆኑን ማየት ያስፈልጋል።

ተፈታኞቹ የመዘጋጃ ጊዜ ሊሰጣቸውና ፈተናው የሚሸፍናቸውን እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል። ድንገተኛ ከሆነ ሌላ ዓላማ አለው ሊያስብል ስለሚችል መጠንቀቅ ያስፈልጋል ሲሉ ያሳስባሉ።

የሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ አስቸጋሪ በሆነበት ወቅት አስጨናቂ በሆነ መንገድ ተፈተኑ መባል የለበትም፣ ድንገተኛም መሆን አይገባውም። ፈታኙ አካልም ራሱን ሊመለከት ይገባል። የፈተናው ዓላማ ማብቃት ከሆነ ወድቃችኋል የሚባልበት ሳይሆን ያሉባቸውን ክፍተቶች ለይቶ ሥልጠና በመስጠት ለማብቃት ዓላማ ሊውል ይገባል ያሉት መምህር ዘላለም።

አማኑኤልም (ዶ/ር) የመምህር ዘላለምን ሃሳብ በመጋራት ፤ በመሠረቱ በፈተና የትምህርት ጥራትን ያመጣ ሀገር የለም። የትምህርት ጥራት መርሁም አይደግፍም። ፈተና የማጥሪያ ስልት ነው እንጂ ጥራትን አያመጣም፤ የጥራት ማሻሻያ አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ።

የትምህርት ጥራትን ለማስተካከል የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። ብቃት ያለው ትውልድ ለማፍራት መምህራን ብቁ ማድረግ፣ ለትግበራውም የመምህራኑን ፍላጎት ማነሳሳት፣ ብቃት ባለው መንገድ እንዲሰለጥኑ ማድረግም ተገቢ ነው ይላሉ። መምህር ዘላለም የተሻለ ብቃትና ውጤት ያላቸው ወደ ማስተማር ሥርዓቱ እንዲገቡና በማስተማር ሂደት ላይ እያሉ ክትትልና ግምገማ ማድረግም ተገቢ ነው። የመምህራንን ጥቅማ ጥቅም ማስጠበቅ፤ ትምህርትን ከፖለቲካ መሳሪያነት መነጠል ይገባል። ጥሩ የሚያስተምሩ መምህራን የሚበረታቱበት ሥርዓት መፍጠር፤ ቸልተኞችን ደግሞ እንዲመከሩ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ይመክራሉ።

አማኑኤልም (ዶ/ር)፤ ትምህርት እና ፖለቲካን መነጠል ያስፈልጋል። የትምህርት አመራሩ ለሙያው ሲመለመል፣ ሲመደብም ሆነ ሲሠራ ከፖለቲካ ነጻ መሆን አለበት። የመማሪያ መጻህፍትና የማስተማሪያ በአግባቡ ሊዘጋጁ ይገባል። የመምህራንን ብቃት ለማሳደግ ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መስጠት ይገባል።

በሁሉም አካባቢዎች የተማሪዎች ምገባ ሥርዓት ማስፈን፣ የትምህርት አካባቢዎች ሳቢና አስፈላጊ ግብዓት የተሟላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ወላጆችም በመማር ማስተማር ሂደት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባልም ሲሉ ያሳስባሉ።

የመምህራንን ችግር በመለየት ክፍተታቸውን ለማረም እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች በትምህርት ጥራት ችግር የደረሰውን ስብራት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሊጠግነው ይችላል። ክትትል ከተደረገና እንዲበቁ ከተደረገ የማይሻሻልበት ምክንያት የለም። ፈተናው ስብራቱን ከሚጠግኑ ጉዳዮች አንዱ እንደመሆኑ መቀጠል አለበት።

የመምህራንን ተገቢ ጥቅምና እድገት በማስጠበቅ የሥራ ፍላጎታቸውን ማነሳሳት፣ በመማር ማስተማር ሂደት ቁጥጥርን (ሱፐርቪዥን) ማጠናከርና የመምህራንን ብቃት ማሳደግ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚለው የሁለቱም መምህራን የጋራ አቋም ነው።

ማስተማር እንደጀመርኩ ትምህርት በሚገርም ቁልቁለት ሲወርድ ተመልክቻለሁ የሚሉት መምህር ዘላለም፤ ስብራቱን ለማስተካከል እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎቹ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። እነዚህ ከተዘነጉ ግን ስጋቱ ከባድ ይሆናል ይላሉ።

በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለሚፈጠረው የተማሪዎች ውጤት ውድቀት ተጠያቂነት ያለው የትምህርት ሕግ ሊተገበር ይገባል። ለተማሪዎችና ለትምህርት ቤቶችና ለሀገር የትምህርት ሥርዓት ውድቀት ተጠያቂ የሚሆን አካል በሌለበት ሁኔታ እየተሠራ የሚቀጥል ከሆነ ችግሩን ማከም አይቻልም የሚሉት ደግሞ አማኑኤል (ዶ/ር) ናቸው።

# የኢትዮጵያ ባሕር በር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሕግ አለመኖሩን ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት በቀጣናው ዘላቂ ሠላምን በማረጋገጥ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

እስከ አሁን ባለው የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚሆን ንግድ የሚካሄደው በባሕር በር በኩል ነው ያሉት አሶሽት ፕሮፌሰሩ፤ ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባህር በር ማግኘት ይጠበቅባታል ብለዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ሀገራት ባሕር በርን የሚያገኙት ከባሕር ዳርቻ (Coastal states) ካላቸው ቅርበትና ባሕር በር ካላቸው ሀገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች በመፍጠር ነው። ይህም የሚሆነው ዓለም አቀፍ ባህር በር አጠቃቀም ሕግ ማንኛውም ሀገር ባሕር በር የመጠቀም መብትን ስለማይከለከል ነው።

በዚህ ሕግ መሠረት ባሕር በር የሌላቸው ሀገራት ባሕር በር ካላቸው ሀገራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ ባሕር በር በመግዛት ወይም አብሮ ባህር በሩን በማልማት የመጠቀም እድላቸውን ያሳካሉ ያሉት ምሁሩ፤ እንደ አሜሪካ፣ ፈረንሳይና መሰል ሀገራት ከሩቅ ተጉዘው ጂቡቲ ወደብ የሚጠቀሙት በዚሁ መልክ ነው ሲሉ እንደ ምሳሌ አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ባሕር በር ከአገኘች ኢኮኖሚዋ በፍጥነት በማደግ አካባቢው ላይ ከፍተኛ ተጸእኖ ታሳድራለች ብለው የሚጠራጠሩ ውስን ሀገራት መኖራቸውን ገልጸው፤ ከዚህም የተነሳ በዓባይ ግድብ ግንባታ እንዳታካሂድ እና ባሕር በር የማግኘት መብቷን እንዳትጠቀም ይፈታተኗታል ነው ያሉት።

ይህም ጫና እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ የዓባይን ግድብ ግንባታ አሳክታለች፤ ባሕር በሩም በተጀመረው ሁኔታ በማስቀጠል ኢኮኖሚውን በፍጥነት በማሳደግ ከተቻለ የማይሳካበት ምክንያት የለም ብለዋል።

እንደ ማትዮስ (አሶሽት ፕሮፌሰር) ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን በፍጥነት ለማሳደግ በትኩረት ልትሠራ ይገባል። ምክንያቱም ኢኮኖሚ በአደገ ቁጥር ወጪ እና ገቢ ምርቶች ይጨምራሉ። የእነዚህ ምርቶች መጨመር የባሕር በር ፍላጎት ከመጨመር ባሻገር ባሕር በር ባለቤቶች ዘንድ ያለውን ተፈላጊነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

ኢትዮጵያ የአፍሪካ መግቢያ በርና የብዙ ዲፕሎማቶች ቢሮ መገኛ በመሆኗ ከአላት ተፅዕኖ ፈጣሪነት አንፃር ባሕር በር አስፈላጊ መሆኑን ገልፀው፤ የቀጣናውን ሠላምና ደህንነት ለማረጋገጥ ባህር በር ተጠቃሚ የመሆን ጥያቄ ውስጥ መግባት አልነበረበትም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ባሕር በር ተጠቃሚነት እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አህጉር በተለይ በምስራቅ አፍሪካ ሠላምን በማረጋገጥና ኢኮኖሚውን በፍጥነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አመልክተዋል።

# ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ኃያላን ሀገራት የነበሩና በኋላ ላይ ያላቸውን ሀብት እና ኢኮኖሚ በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ምክንያት ወደ ደሃ ሀገራት ተርታ ተሰልፈው ነበር፡፡

ድህነት፣ ሥራ አጥነት እና በምግብ እጥረት ዜጋቸው የሚሞትባቸው ሀገራት እንደነበሩ ተናግረው፤ ሀገራቱ ያሉባቸውን ችግሮች በምርምር ለይተው በማወቅ ኤክስፖርትን መሠረት ያደረገ ኢንዱስትሪያላይዜሽን ውስጥ መግባታቸውን ነው የገለጹት፡፡

እነዚህ ሀገራት የምርት ጥራት በመጨመር ለውጭ ሀገራት ኤክስፖርት ማድረግ ላይ ትልቅ ሥራ በመሥራት ትልቅ የኢኮኖሚ ለውጥ ማምጣታቸውንም ያብራራሉ፡፡

እንደ ለገሰ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ሀገራቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሥርዓት በመከተልም የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ታክስ በመቀነስ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ሀገራቸው መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ አስችለዋል፡፡ እንዲሁም ሀገራቱ ምርቶች በሀገራቸው ላይ እንዲመረቱ ማድረጋቸው የውጭ ምንዛሪ በማዳን ዜጎቻቸው የሥራ እድል እንዲያገኙ ማድረጉንና ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ እንዳገዛቸው ጠቁመዋል፡፡

የትምህርት ጥራት ላይ እና ለሳይንስ ትኩረት በመስጠት በሰው ሃይል ላይም ከፍተኛ ሥራ መስራታቸውን አውስተው፤ የተማሩ ወጣቶችን ወደ ሌሎች ሀገራት ጭምር ሄደው እንዲሠሩ ማድረግ መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

መሠረተ ልማት ግንባታ ፣ የኮሙኒኬሽን ሥርዓት ማሳደግ፣ ኢንዱስትሪያላይዜሽን፣ ኔትዎርክ ዝርጋታ እንዲሁም መንገዶችን ላይ በሚገባ መሥራታቸውን አመልክተው፤ አረንጓዴ ልማት ላይም በሚገባ በመሥራት በርሃማ አካባቢዎችን በመቀየር ለሌሎች ሀገራት አርዓያ መሆን መቻላቸውን ያስረዳሉ፡፡

የእርሻ ሥራን በማዘመን በሚገባ በመሥራት በዓለም አቀፍ ገበያው ላይ ተጽዕኖ መፍጠር መቻላቸውን የተናገሩት ምሁሩ፤ ጥሩ የአየር ጸባይ እና መሬት ያላቸው አፍሪካውያን ጭምር ሩዝ እና ሌሎች የሰብል ውጤቶችን ከእነዚህ ሀገራት በማስገባት እንደሚጠቀሙ አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሀገራት ብዙ መማር እንደምትችል ተናግረው፤ አንደ ሀገር ኢኮኖሚዋን ለማረጋጋት በቅድሚያ ሰላም እና ጸጥታ ላይ መሥራት አለባት ይላሉ፡፡

"ኤዢያን ታይገርስ" የሚባሉት ሀገራት ከነበረባቸው የዕርስ በርስ ግጭት ወጥተው ኢኮኖሚያቸውን ማሳደጋቸውን ተናግረው፤ ኢትዮጵያውያንም ግጭት ኢኮኖሚያችንን ወደ ባሰ ሁኔታ እንደሚወስድ በመረዳት ሰላም በማምጣት ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ መሥራት አለብን ነው ያሉት፡፡

የትምህርት ጥራት ላይ፣ ዲጅታል ኢኮኖሚው ላይ ፣ በባንክ ኢንዱስትሪው፣ በቴሌኮም ዘርፍ እና በብሔራዊ መታወቂያ ላይ በኢትዮጵያ የተጀመሩ ሥራዎች መጠናከር እንዳለባቸው ገልጸው፤ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችም ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው የሚል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከእነዚህ ሀገራት የሥራ ባህል በሚገባ መማር አለብን የሚሉት ለገሰ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያውያን ሥራን ለነገ ብለን ማስቀመጥ ማቆም አለብን ሲሉ ሃሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

ሌላኛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ በጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን ያጋሩት የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ መምህር አቶ ሀብታሙ ለገሰ እንደተናገሩት፤ የ "ኤዢያን ታይገርስ" ሀገራት ኤክስፖርት እና ኢንዱስትራላይዜሽን ላይ ከፍተኛ የሆነ ሥራ መሥራታቸው ትልቅ የኢኮኖሚ እድገት እንዲያስመዘግቡ ምክንያት ሆኗቸዋል ባይ ናቸው፡፡

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ ሀገራቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቧቸውን ምርቶች በራሳቸው ምርት መተካታቸው፣ ቁጠባቸውን ማሳደጋቸው ፣የሰው ሀብት ልማት ፣ ጤና እና ትምህርት ላይም በከፍተኛ ሁኔታ መሥራታቸው ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግቡ አድርጓቸዋል፡፡

አሁን ላይ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገቷን ለማሻሻል የሰላሟን ሁኔታ ማስተካከል እንዳለባት ጠቁመው ፤ኤክስፖርት ለማሳደግ መጀመሪያ ምርት ማሳደግ የሚያስፈልግ በመሆኑ ምርት ማሳደግ ላይ በቅድሚያ መሠራት አለበት ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያደገ መሆኑን ገልጸው፤ በዋናነት እያደገ የመጣው የትምህርት፣ የጤና እና የባንክ ዘርፎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመሆናቸው ማኑፋክቸሪንግ ላይ የተሠማሩ አካላትን ታክስ በመቀነስ ማኑፋክቸሪንግን ማሳደግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የቁጠባ ባህላችንንም ማሳደግ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ትምህርት ላይም መንግሥት በሚገባ የሚያስፈልገውን ዘርፍ በማጥናት ትኩረት ሰጥቶ ኢንቨስት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ነው የጠቆሙት፡፡

ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት እንደሚያስፈልግ ተናግረው ፤ መንግሥት የሚያስመጣቸው እንደ ማዳበሪያ እና ስኳር የመሳሰሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት እንዳለበትም ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

በመንግሥት ደረጃ ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች እያሉ የውጪ ምርቶች እንዳይገቡ የተጀመሩ የማገድ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም ገልጸዋል፡፡

ሥራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ከምርት እጥረት ጋር የተያያዙ ችግሮች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ምርት እንዲጨምር መሥራት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ እነኚህ ሀገራት የደረሱበት ለመድረስ የሰላሙን ሁኔታ ማሻሻል፣ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ በሚገባ መሥራት፣ ለማኑፋክቸሪንግ የምትሰጠውን ትኩረት መጨመር እንዳለባት ተናግረው፤ በፖሊሲ የሚስተካከሉ ነገሮች ከተስተካከሉ እና ኢኮኖሚው በእውቀት ከተመራ ከእነዚህ ሀገራት ፍጥነት በተሻለ የኢኮኖሚ እድገት ልታስመዘግብ እንደምትችልም ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛቷ ፣ በዲፕሎማሲ እና በቢዝነስ ማዕከልነትዋ ትልቅ ሀገር ናት፡፡ እንደ ሀገር ከሆንግ ኮንግ፣ ከሲንጋፖር፣ ከታይዋን እና ከደቡብ ኮሪያ በመማር ያላትን የሰው ሃይል፣ የተፈጥሮ ሀብት እና ለም መሬት ከተጠቀመች ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ከተካች፣ ምርት በመጨመር እና ኤክስፖርት በማሳደግ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ትችላለች ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ልኡካን ቡድናቸው እስያ ታይገር ተብሎ ከሚጠሩት አራት ሀገሮች በደቡብ ኮሪያና በሲንጋፖር ይፋዊ የሥራ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በጉብኝታቸውም ከሁለቱ ሀገራት ጋር ግንኙነታቸውን ለማጠናከር የተለያዩ ስምምነቶችን ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአረንጓዴ ዐሻራ ያስመዘገብነውን ስኬት ወደ ላቀ ደረጃ እናሸጋግር!

ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሞገስ እና ተደማጭነት ካገኘችባቸው አጀንዳዎች አንዱ የአረንጓዴ አሻራ ነው። ይህ ሀገርን አረንጓዴ እናልብስ በሚል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት በተፈጠረ ሀገራዊ መነቃቃት በ2011 ዓ.ም የተጀመረው የችግኝ ተከላ ዘመቻ የተራቆቱ መሬቶችን በደን ከመሸፈን ባለፈ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ሀገሪቱ ሊያጋጥማት የሚችለውን ፈተና ለመሻገር የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል።

በርግጥ ኢትዮጵያውያን ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ የዛፍ ችግኞችን የመትከል ልማድ እንዳላቸው በየዘመኑ የነበሩ ነገስታቶችም ለችግኝ ተከላ ትኩረት ሰጥተው መሥራታቸውን የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።ይህም በተወሰነ መልኩ የሀገሪቱን የተፈጥሮ አካባቢ መጠበቅ እንዳስቻለ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በዘመናት ሂደት ውስጥ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የከተሞች መስፋፋት ፣ የሚታረስ መሬት መጨመር ... ወዘተ የደኖች ምንጣሮ መብዛቱና እነሱን የመተካቱ ጥረት ዝቅተኛ መሆን ሀገሪቱን ከፍተኛ ለሆነ የደን መራቆት ዳርጓታል። ከዚህ ጋር በተያያዘም ዓመታት ቆጥሮ ለሚመጣ የድርቅ አደጋ ተጋላጭ የሆነችበት ፣ ሰፊ የሚባል የተፈጥሮ አካባቢም ለአደጋ የተጋለጠበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

"በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው" የደን መራቆት ችግሩ ዓለምን እየተፈታተነ ካለው ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቅ ካርቦን ጋር ተዳምሮ ሀገሪቱን የከፋ የተፈጥሮ አደጋ ስጋት ውስጥ ሊከታት እንደሚችል፤ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጅት መፍጠር ካልቻለች አጠቃላይ በሆነው የሕዝቦቿ የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ሊያሳድር የሚችለው አደጋ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይገመታል።

አሁን ላይ በግብርና ላይ የተመሰረተው የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ጨምሮ በምግብ እህል አቅርቦት ላይ ሊያሳድር የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ እንደ ሀገር በጀመርነው ራሳችንን በምግብ እህል ለመቻል የጀመርነውን ሀገራዊ ንቅናቄ የሚፈታተን ፣ ከዚህም በላይ ድህነትን ታሪክ አድርገን ለመሻገር የጀመርነውን መራራ ትግል ትርጉም አልባ ሊያደርገው እንደሚችል ይታመናል።

ይህንን ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስጋት ለመከላከል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሃሳብ አመንጪነት በተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ከ32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል።

በቀጣይ ሦስት ዓመታት ደግሞ 17 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በመትከል 50 ቢሊዮን ችግኞችን በስምንት ዓመታት ውስጥ ለመትከል እቅድ ተይዟል። እስካሁን ለተተከሉት ችግኞች በተደረገው ክትትል እና እንክብካቤ የችግኞቹ የጽድቀት መጠን ከ90 በመቶ በላይ ደርሷል። ለዚህም መላው ሕዝብ ችግኝ ከመትከል ባለፈ እያዳበረ የመጣው የመንከባከብ ሥራ ትልቁን ስፍራ የያዘ ነው።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በዘንድሮ ዓመት አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል። የችግኝ ቁጥር በሄክታር ሲሰላ ዘንድሮ ተከላ የሚደረግበት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንደሚሆን ይገመታል።

የመላው ሕዝባችን የነቃ ተሳትፎ የታየባቸው በእነዚህ አምስት ዓመታት ሕዝባችን ከሁሉም በላይ የችግኝ ተከላ ለራሱም ሆነ ለመጪዎች ትውልዶች እጣ ፈንታ የቱን ያህል ወሳኝ አቅም እንደሆነ በአግባቡ መረዳት የቻለበት፣ ከዚህ በመነሳትም ኃላፊነት በሚሰማው መንገድ የሚጠበቅበትን ለማድረግ በንቃት የተንቀሳቀሰበት ነው።

የችግኝ ተከላው በሂደት ለምግብነት የሚውሉ የአትክልት እና ፍራፍሬ ችግኞችን ታሳቢ እያደረገ መምጣቱ እንደ ሀገር በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል ለምናደርገው ሀገራዊ ንቅናቄ ስትራቴጅክ አቅም መሆን የቻለ ነው። እንደ ሀገር ያለብንን የተመጣጠነ የምግብ እህል አቅርቦት ችግር ለመፍታትም ሌላኛው አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ከዚህም ባለፈ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ብዛት ያለው የሰው ኃይል ችግኝ ከማፍላት ጀምሮ ባለው የሥራ ሂደት ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ እንደ ሀገር ያለብንን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ለሚደረገው ጥረት ተጨባጭ አቅም የሆነበት ሁኔታም ተፈጥሯል። በዚህም ብዛት ያላቸው ዜጎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በዚህ ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለስድስተኛ ጊዜ የምናካሂደው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርም ይህንን በዘርፉ እንደ ሀገር እያስመዘገብን ያለውን ትልቅ ስኬት በማስቀጠል ወደላቀ ደረጃ በማሸጋገር ሀገራዊ ተጠቃሚነታችንን ማጎልበት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያገኘነውን ዕውቅናና ተደማጭነት በተሻለ መልኩ ማስቀጠል የሚያስችል ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያዊ መልካችን ይሻለናል!

ሶሎሞን በየነ

እንደሚታወቀው በመፅሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁራን ውስጥ በተደጋጋሚ ስማቸው ከተጠቀሱ የዓለም ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ ከግንባር ቀደሞቹ ተርታ ትሰለፋለች። ይህም የሚያሳየው ሀገሪቱ ጥንታዊ የእምነት፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የፍልስፍና የሥነ-ጽሁፍ፣ የዜማ፣ የጥበብ ... ወዘተ መፍለቂያ መሆኗን ነው። ሕዝቧም ከዓለም ሕዝብ ቀድሞ የሠለጠነ፣ የሥልጣኔ ፈር ቀዳጅ መሆኑን ነው።

ለአብነት "ኢትዮጵያ" የሚለው የሀገራችን ስም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ 43 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። በቅዱሱ መፅሐፍ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከተነገሩት ታሪኮች ውስጥ ለዛሬ መጣጥፌ መንደርደሪያ ይሆነኝ ዘንድ፤ ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 13 ከቁጥር 23 ላይ ያለውን ታሪክ ወስጃለሁ። በዚህ ገጽ ላይ "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?" የሚል ሃይለ ቃል ተፅፎ እናገኛለን።

አዎ! ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው ዛሬም ድረስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን አልለወጠም። ነብር ባሕሪውን አልቀየረም። ዛሬም የሚኖረው በጫካ ነው። አመጋገቡም እንደጥንቱ አልተቀየረም። የዚህን እንስሳ የተራክቦ ሥርዓት ብንመለከት፤ ከግልገልነታቸው ጀምሮ አብረው ካደጉ በኋላ ባልና ሚስት ይሆናሉ። ልክ እንደሰው ልጆች ወልደው ተንከባክበው ያሳድጋሉ። በፍቅር ይኖራሉ።

በሕይወት እያሉ ነብር ከሚስቱ ወይም ከባሏ ውጭ አይባልግም/ አትባልግም። ከሁለት አንዱ በሞት ቢለይ፤ በሕይወት የቀረው ወይም የቀረችው በዱር፣ በገደሉ መንኖ ወይም መንና ከእንስሳ ተገሎ/ላ እስከ ሕይወት ፍሜው ወይም ፍጻሜዋ መንኩሳ/ሶ ይኖራል ወይም ትኖራለች። ዛሬም ይህ እንስሳ ፀባዩን፣ ባሕሪውን፣ አኗኗሩን፣ ... ወዘተ አልቀየረም።

ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ከእንስሳ አንሰን መልካችንን ቀይረናል። አዎ! መልካችን ተቀይሯል። ደም ግባታችን ከገጻችን ጠፍቷል። ውበታችን እረግፏል። የሚያምረው መልካችን ተጠብሷል፣ በልዟል፣ ከስሷል፣ ተበርዟል። በጥቅሉ ባሕሪያችን፣ መልካችን፣ ማንነታችን፣ ፀባያችን ... ተለዋውጧል።

ኢትዮጵያዊ መልካችን ምን ነበር? ብለን ስናወሳ ከየት መጣህ? ዘርህ፣ ቋንቋህ፣ ቀለምህ፣ መልክህ ... ምንድ ነው? ሳይል በፍቅርና በፈገግታ እንግዳ ተቀብሎ እግር አጥቦ፣ ቤት ያፈራውን "በሞቴ ብሉልኝ፣ ጠጡልኝ" ብሎ አብልቶ፣ አጠጥቶ፣ ከሳጥን የታጠበውን አውጥቶ አልብሷ፣ አልጋውን ለእንግዳ ለቆ መሬት ላይ ተኝቶ ማስተናገድ ነበር።

በተለይ በከተሜው ልክ እንደዛሬው ለአውደ ዓመት አርዶ በፍሪጅ የሞተ ሬሳ ሥጋ ከቶ ቤት ዘግቶ ብቻ መብላት ሳይለመድ፤ የዛሬን አያድርገውና ድሮ ለአውድ ዓመት ታርዶ፣ ጠላ ተጠምቆ፣ ጠጄ ተጥሎ፣ ጎረቤት፣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ ተጠርቶ፣ "ብሉልኝ፣ ጠጡልኝ" ተብሎ ነበር በጋራ የሚበላው፣ የሚጠጣው። ይሁን እንጂ የሀገሬው ሕዝብ ይህን በማድረጉ ማድጋው ጎሎ፣ ማሰሮው ነጥፎ፣ ጓዳው ተራቁቶ አያውቅም ነበር። ይህ ነበር መልካችን፣ ወግ ልማዳችን።

እርስ በእርስ አንተ ትብስ አንቺ ተባብለን ተከባብረን በመኖር፤ ድንበር ጥሶ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነታችን ሊያጠፉ የመጣን ጠላት ልክ ቀፎው እንደተነካ ንብ "ግልብጥ" ብሎ ወጥቶ በተደጋጋሚ በጋራ ድል የነሳን፤ ከነኩን ወደ ኋላ የማንል፣ ክንደ ብርቱዎች፣ ልክ እንደ አንበሳ የተፈራንና የተከበርን ነበርን።

የኛ ኢትዮጵያውያን የጥንት የጧቱ መልካችን፣ ውበታችን፣ ባሕሪያችን ... የታረዘን ማልበስ፣ ፍትህ የተጓደለበትን መካስ፣ ስደተኛና እንግዳ መቀበል፣ በጋራ መቆም፣ ሃይማኖትን ከምግባር ጋር መኖር፣ በቃል መገኘት፣ መደጋገፍ፣ መተሳሰብ፣ መተባበር፣ መተዛዘን፣ መፈቃቀር ... ነበር። አንድነትና ፍቅራችን የሃይላችን ሚስጥር፤ የአልበገርነት ባይ መገለጫችን ነበር።

ይሁን እንጂ ይህንን የሃይላችን፣ የሰላማችን፣ የፍቅራችን፣ የአልደፈር ባይነታችን፣ የአንድነታችን... ሚስጥር የሆነውን ኢትዮጵያዊ መልካችን አጥብቀን ባለመያዛችን፤ በዚህ በሉላዊ ዓለም በእየለቱ ከሚፈጠሩ ተለዋዋጭና መጤ ባህሎች ሳቢያ በሂደት ኢትዮጵያዊ መልካችን፣ ባሕሪያችን፣ ፀባያችን ተቀይሯል፣ ተበርዟል። ደም ግባታችን ፈዝዟል ።

በዚህም አንተ ትብስ አንቺ ተባብሎ ተከባብሮ መኖር ተስኖን፤ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ከእርስ በእርስ የጦርነት አዙሪት መውጣት አቅቶናል። በእርስ በእርስ ጦርነት የአንድ እናት ልጆች እልፍ በግራ፣ እልፍ በቀኝ ወድቀዋል፤ እየወደቁም ይገኛሉ። በተለይ ከ1966ቱ አብዮት በኋላ በሀገሪቱ ሰላም ጠፍቷል፤ የእርስ በእርስ ጦርነት ነግሷል፣ መገዳደል በዝቷል። በጥቅሉ ምድር አኬል ዳማ ሁናለች። ወንድምን ገድሎ በወንድም እሬሳ ላይ መፎከር የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሆኗል።

ባህር አቋርጦ የመጣን እንግዳ ባህል፣ እምነቱን አክብሮ ተቀብሎ ተንከባክቦ ያኖረ ማህበረሰብ፤ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያዊ መልኩ ተቀይሮ ትናንት ለሀገራቸው ዳር ድንበር አብረው የተዋደቁ ወንድማማቾች በዘርና በቋንቋ ጎራ ለይተው አንዱ አንዱን እያፈናቀለ፣ እየገደለ፣ እያሳደደ ይገኛል።

አብዛኛው የኃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በንዋይ አይናቸው በመታወሩ፤ እውነተኛ የሃይማኖት አባት፣ የሀገር ሽማግሌ ጠፍቷል። በእምነቱ የጸና፣ ለቃሉ የታመነ ምዕመን ጠፍቷል። አብዛኛው ማህበረሰብ አንድ ዳቦ በልቶ ለማደር ተቸግሮ፤ ጥቂቶች "ከየት አመጡት" ብሎ ጥያቄ በሚያስነሳ መልኩ ከህንፃ ላይ ህንፃ ይደረድራሉ።

እነዚህ አካላት ከነዋይ ሌላ የሀገርና የወገን ፍቅር የላቸውም። በወገን ደምና ላብ የሚነግደው ስግብግብ ነጋዴው በዝቷል። በጥቅሉ ከ90 ከመቶ በላይ አማኝ ሕዝብ ባለበት ሀገር የሚፈጸሙ ወንጀሎች ለመስማት ይዘገንናሉ። ሰላም፣ ደስታ፣ እርቆናል በአንጻሩ የሞት፣ የረሀብ፣ የችግር፣ የጦርነት ዜና ዙሪያችን ከቦናል።

ስለምን ደስታ፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ልማት፣ እድገት፣ ከኛ እራቀ? በተቃራኒው ስለምን ሞት፣ ረሀብ፣ ችግር፣ ጦርነት በሀገራችን ነገሰ? ብለን ሁላችንም እራሳችንን ቆም ብለን ብንጠይቅ እንደኔ ኢትዮጵያዊ መልካችንን በመቀየራችን ነው። በመሆኑም በፍቅር፣ በደስታ በሰላም፣ ተከባብሮ ለመኖር እና ሀገራችንን ከገባችበት የጦርነት አዙሪት ለማውጣት ከመቼውም ጊዜ በላይ ኢትዮጵያዊ መልካችን ያስፈልገናል።

ሁሉም ዜጋ አንድነትና ፍቅራችን ከሚሸረሽሩ የምዕራባውያን ባህልና ወግ እራሱን አላቆ፤ ልክ እንደ ንስር ኢትዮጵያዊ መልካችን አድሰን በከፍታው ማማ እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንወጣ ይገባል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ሁሉም ዜጋ ኢትዮጵያዊ መልኩን በተግባር ሊኖረው ይገባል።

የእምነት አባቶች ደግሞ ልክ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ለሀገር ሰላም፣ ለወገን ፍቅርና አንድነት፣ ለሃይማኖት ዶግማና ቀኖና መከበር አንገታቸውን ለሰይፍ፤ ደረታቸውን ለጦር ሊሰጡ ይገባል። በጥቅሉ በሰላም ተከባብሮ ለመኖር ኢትዮጵያዊ መልካችን ይሻለናል፤ ይበጀናል!

# ነፃ ሃሳብ

# አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብ እና አዲስ የማድረጉ የልማት ጉዞ

**እስማኤል አረቦ**

ከ135 ዓመታት በላይ ያስቆጠረችው አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ እና ውብ ሳትሆን ዘመናትን ተሻግራለች። እንዲውም ከስሟ በተጻራሪ የቆሻሻ እና የብክለት ተምሳሌት ሆና ያለፉትን ዘመናት አስቆጥራለች። በውልደትና በስደት በየጊዜው የሚያሻቅበውን የሕዝብ ቁጥር የሚመጥን የመኖሪያ ቤትና ሌሎች ተያያዥ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት ባለመቻሏም ከፍተኛ ሆነ ጉስቁልና የሚታይባት ከተማ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

በተለይም መሐለኛው የአዲስ አበባ ክፍል ችምችም ብለው በተሠሩ ቤቶች የታጨቀ፤ ከዘመኑ ጋር ያልዘመነ፤ ከ135 ዓመታት በፊት በነበረው የቀጠለ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን የአኗኗር ሁኔታ የማይመጥን ነው። አብዛኞቹ ቤቶች አንድ መፀዳጃ ቤትን ለሠላሳ፤ ለአርባ የሚጠቀሙ ብዙዎችም መፀዳጃ ቤት የሌላቸውና በየጥጋጥጉ ለመጠቀም የተገደዱ ዜጎች ያሉባቸው አካባቢዎች ናቸው።

ልብ ብሎ ላየው ይህ አኗኗር ልብን የሚሰብር ነው። በዚህ ዘመን ሰዎች አንድ መፀዳጃ ቤትን ለሠላሳ እና ለአርባ ሲጠቀሙ፤ ከዝናብም ሆነ ከፀሐይ በማያድኑ በተጎሳቀሉ ቤቶች ውስጥ ዜጎች ተደራርበው ሲኖሩ ሲታይ መንፈስን ያውካል። በእነዚህ ጎስቋላ ሰፈሮች ሴተኛ አዳሪነት፤ ጎዳና ተዳዳሪነት፤ ዝርፊያና ግድያ ተንሰራፍቶ ከመገኘቱም በላይ የዜጎች በሠላም ወጥቶ የመግባቱ ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ ሆኖ መገኘቱ ጉዳዩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ያደርገዋል።

ፒያሳን የመሳሰሉ አካባቢዎች ስማቸው ገናና ቢሆንም በገቢር ግን ስማቸውን የሚመጥን ገጽታ የላቸውም። ምንም አይነት ዘመናዊነት የማይታይባቸው ኋላቀር አካባቢዎች ከመሆናቸውም በላይ በስመ አራዳ ለዘመናት ድህነት ተጭኗቸው የቆዩ ናቸው።ስምና ግብር በተራራቀበት በእነዚህ ሰዎች በአንዲት ክፍል ውስጥ ቆጥና ምድር ሠርተው፤ መፀዳጃ ቤት ተጋርተው፤ በአንዲት ክፍል አስር፤ አስራ አምስት ሆነው ተደራርበውና ተነባብረው የሚኖሩባቸው የድህነት ጥግ የሚታይባቸው የከተማችን አካል ናቸው ፡፡

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ እና የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ክብሯንና ከፍታዋን የሚመጥን ገጽታና መሠረተ ልማት ሳይሟላላት ዛሬ ላይ ደርሳለች። ከዚህ በላይ መቀጠል የከተማዋን የአፍሪካ መዲናነትና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡

እነዚህንና ሌሎች ማኅበራዊና ኢኪኖሚያዊ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት ከተማዋን እንደስሟ ውብና አዲስ ለማድረግ ቀርቶ ከተነሳ ወራቶች ተቆጥረዋል። ከተማዋ ካለባት የመሠረተ ልማት እጥረት እና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ እንዲሁም ዘመናት ያስቆጠሩ መሠረተ ልማቶችን ለማዘመን፣ ለማደስ እና የነዋሪዎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የኮሪደር ልማት ማከናወን መጀመሩ ይታወቃል፡፡

በመጀመሪያ ዙርም በዓድዋ ድል መታሰቢያ ፒያሳ-አራት ኪሎ-ቀበና-መገናኛ፤ አራት ኪሎ-ቦሌ አየር ማረፊያ-ቦሌ ድልድይ-መገናኛ፤ ከመገናኛ-አዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ማዕከል ሲኤምሲ እንዲሁም ከሜክሲኮ-አፍሪካ ኅብረት-ሣር ቤት ወሎ ሰፈር 40 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች ወደ ግንባታ ገብተው አብዛኞቹ መንገድ፤ የኤሌክትሪክ፤ የውሃና የቴሌ መሠረተ ልማቶች ወደ መገባደዱ ደርሰዋል። በተለይም ከፒያሳ እስከአራት ኪሎ ያለው መንገድ አብዛኞቹ መሠረተ ልማቶች ተሟልተውለት የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ደርሷል፡፡

በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት ሥራዎችን ያየ ከሚደመምባቸው ተግባራት አንዱ የእግረኛ መንገዶች ስፋትና የአረንጓዴ ልማት ተጠቃሾች ናቸው።አንድ ከተማ ለነዋሪዎች ምቹ እና ዘመናዊ ነው የሚባለው የተስተካከለ የመንቀሳቀሻ መንገዶች ሲሟሉ ጭምር በመሆኑ የእግረኛ መንገዶቹ ስፋት ፈረስ የሚያስጋልብ የሚባል አይነት እየሆነ ነው

የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ብስክሌትና ሌሎች የመዝናኛና የእግር ጉዞ እንዲሁም ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ማዘውተሪያ ስፍራዎችን የሚይዝ በመሆኑ አዲስ አበባ ያላትን አሕጉራዊና ዓለም አቀፍ ደረጃዋን ከፍ የሚያደርግ ነው። በኮሪደር ልማት ሥራው ቀደም ሲል የነበሩ ሕንጻዎች በመታደሳቸውና አንዳንዶቹም የቅርጽ ለውጥ በማድረግ ጭምር ውብና ማራኪ እንዲሆኑ በመደረጋቸው ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት መፍጠር ችለዋል። የሕንጻዎቹ የቀለም ቅብና ፅዳት ዓይን በሚማርክ መልኩ ተውቧል። በቀጣይም የሚሠሩት ሕንጻዎች ዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥቶላቸው በዘመናዊ መልኩ ስለሚገነቡ አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ የምትሆንበት ቀን ሩቅ አይሆንም።

በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት ሥራዎችን ያየ ከሚደመምባቸው ተግባራት አንዱ የእግረኛ መንገዶች ስፋትና የአረንጓዴ ልማት ተጠቃሾች ናቸው። አንድ ከተማ ለነዋሪዎች ምቹ እና ዘመናዊ ነው የሚባለው የተስተካከለ የመንቀሳቀሻ መንገዶች ሲሟሉ ጭምር በመሆኑ የእግረኛ መንገዶቹ ስፋት ፈረስ የሚያስጋልብ የሚባል አይነት እየሆነ ነው። ከእግረኛ መንገዶቹ ጎን ለጎን ክፍት ቦታዎች በአበቦችና በዘንባባ ዛፎች አምረውና ተውበው ሲታዩ መንፈስን ያረካሉ፤ ልብን ይሞላሉ። ለወትሮው በዘንባቦች ውበትና በአበቦች ድምቀት የማትታወቀው አዲስ ዛሬ አይን ማራኪ በሆኑ አፀዶች ደምቃ ለሥራም ሆነ ለኑሮ ምቹ ሆናለች፡፡

እነዚህ ሁሉ ልማቶች ሲከናወኑ ታዲያ ነዋሪውን ታሳቢ በማድረግ ነው። ልማቱ ከመጀመሩ በፊት በአግባቡ በማወያየትና ከተጀመረ በኋላ እንደነዋሪው ፍላጎት የኮንዶሚኒየም ቤትና የቀበሌ ቤት በመስጠት ጭምር ልማቱን ያለምንም ቅሬታ ሕዝቡ እንዲቀበለው ለማድረግ ተሞክሯል። ለግል ቤት ነዋሪዎችም ካሳና ምትክ ቦታ በመስጠት ልማቱ ሁሉንም የሚጠቅም መሆኑን በገሐድ ታይቷል፡፡

የነዋሪዎችን ማኅበራዊ ትስስር ለማስቀጠልም በድጎማ የሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል መኖሩም አብሮነታቸውን ለማስቀጠል ምቹ አጋጣሚ ነው። ይህም ልማቱ የማኅበረሰቡ ማኅበራዊ መስተጋብር እንዲቀጥልና በልማቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጥርባቸው የሚያደርግ ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የኮሪደር ልማቱ ታሪካዊ ቦታዎች እንዲሁም ቅርሶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መከናወኑ አድናቆት የሚገባው ነው። በተቻለ መጠን ነባር የከተማዋ አካባቢዎች ሲፈርሱ ቅርሶች እንዳይፈርሱ ጥንቃቄ በማድረግ መሠራቱ አዲስ አበባ የጥንት ገጽታዋን ሳትለቅ ከዘመናዊው ጋር እንደትዋሓድ አስችሏታል፡፡

በቅርስነት የተለዩ እንደሲኒማ ኢትዮጵያ፣ ሀገር ፍቅር፣ ሸዋ ሆቴል፣ ሲቲ ኮንቬንሽን፣ የሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ቤት፣ የቀድሞዎቹ ማዘጋጃና ፖስታ ቤት ታድሰው ባሉበት ይቀጥላሉ ተብሏል። ይህም አልፎ አልፎ በአንዳንድ «አክቲቪስቶች» ዘንድ የሚነዛውን የሐሰተኛ መረጃ ያከሸፈ ነው፡፡

የኮሪደር ልማቱ እስካሁን ከተሠሩት የልማት ሥራዎች መካከል ማዘጋጃ ቤት፣ መስቀል አደባባይ፣ ወንድማማችነትና አንድነት ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም አብርኆት ቤተ መጽሐፍት፣ ጎተራ አቃቂ ቦሌ መንገድ ግንባታ በመሳሰሉ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ላይ ተጨማሪ ውበትን የሚፈጠር ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና ድንገተኛ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መረጃ እንደሚያመላክተው፤ የመዲናዋ የኮሪደር ልማት ከከተማ ልማትም ባለፈ ለእሳትና ድንገተኛ አደጋ ተጋላጭ የነበሩ ዜጎችን ሊታደግ የሚችል ነው። በተለይም ነባር በሆኑት የከተማዋ ክፍሎች የኤሌክትሪክ ዝርጋታው እጅግ ኋላቀር ከመሆኑ በላይ እጅግ የተወሳሰበና ለአደጋም የተጋለጠ ነው፡፡

በዚህ ላይ ዝናብና የንፋስ ሽውታ ሲያገኘው በቀላሉ የሚበጠስና መብራትም በየአጋጣሚው የሚጠፋበት አካባቢ ነው። ንፋስና ዝናብ ሲመጣ በቀላሉ በኤሌክትሪክ ዝርጋታው ላይ አደጋ ስለሚደርስ እሳት ቃጠሎን የመሳሰሉ በሰዎች ሕይወትና በንብረት ላይ የከፋ አደጋ ሲደርስ ቆይቷል፡፡

በኮሪደር ልማቱ የኤሌክትሪክ መስመሮች ከምድር ውስጥ ስለሚቀበሩ ለዘመናት ሲደርስ ነበረውን አደጋ ሙሉ ለሙሉ የሚያስቀር ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም በየኪሎ ሜትሩ የእሳት አደጋ ማጥፊያ ውሃ ስለተቀበረ በቀላሉ አደጋ ሲደርስ ቀድቶ አደጋውን በቀላሉ መታደግ የሚያስችል ዕድል ፈጥሯል፡፡

በዚህ ረገድ ከቤቶች ግንባታ ጥግግት፣ ከመንገዶች ጥበት፣ ከኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ገመዶች መደራረብ እና ከፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች መደፈን ጋር የሚከሰቱ አደጋዎችንም ለመከላከል እየተከናወነ ያለው የመንገድ ኮሪደር ልማት የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው። የኮሪደር ልማቱ ቤቶች በፕላን እንዲገነቡ፣ መንገዶች እንዲሰፉ፣ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታና የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በጥራት እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው።

በርካታ አካባቢዎችን ከእሳት ቃጠሎ፣ ከጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ከትራፊክ መጨናነቅና ሌሎችም አደጋዎች የታደገ ሁነኛ መፍትሔ ይሆናል ተብሎም ይታመናል። በየዓመቱም በትራፊክ አደጋ የሚቀጠፈውንም ሕይወት ለመታደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። በጤና ረገድም የሚጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም የውሃ ማስተላለፊያ መስመሮችና የቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦዎች የተቀበሩበት ሁኔታ ኋላ ቀርና የጤና ችግርም የሚያስከትል ነው። አብዛኞቹ ውሃ መስመሮች ከቱቦዎች ጋር መሳለመሳ የተቀበሩ በመሆናቸው ከመፀዳጃ ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ከሚጠጣው ውሃ ጋር እየተደባለቀ ለከፋ የጤና ችግር ሲዳርግ የቆየ ነው፡፡

አብዛኞቹ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች የተቀበሩት ከከተማዋ ምሥረታ ጋር በተያያዘ በመሆኑ ከማርጀታቸውም ባሻገር አሁን ያለውን የሰው ቁጥር የማስተናገድ አቅም የላቸውም። በዚህም ላይ በየጊዜው በሚሠሩ ግንባታዎች አማካኝነት ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎቹ ለብልሽት ስለተዳረጉ በአግባቡ ፍሳሽን የማስወገድ አቅም ተስኗቸዋል። በዚህም ምክንያት አካባቢዎቹ በየጊዜው በሚፈነዱ መፀዳጃ ቤቶች የሚጥለቀለቁና አፍንጫ በሚሰነፍጥ ጠረናቸውም የሚታወቁ ናቸው። ይህ ደግሞ ለአስምና ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች መንስኤ ሲሆን መቆየቱ የሚታወስ ነው፡፡

የኮሪደር ልማቱ ከተሞች በቴክኖሎጂ የዘመኑ እንዲሆኑ እና ተመራጭ የቱሪዝም እና የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንዲሆኑም ያስችላል። ንግድና እና የትራንስፖርት ቀልጣፋ ያደርጋል። ይህም የዜጎች ሕይወት እንዲሻሻል፣ ከተሞች ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆኑ እና ሀገር እንድትበለጽግ በር ይከፍታል፡፡

በአጠቃላይ በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያከለው ኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሠረቱ የሚቀይር ነው። ከሁሉም የሚያስደስተው ደግሞ ሥራውን በታያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚደረገው ርብርብ አግራሞትን የሚፈጥር ነው። አጠቃላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለተመለከተ የኮሪደር ልማቱ በታሰበለት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መገመት አያዳግትም።

ኢኮኖሚ


# ግብርና




የሩዝ ቡቃያ



ኢንጂነር አብዱዋሂድ ሙሂዲን



አቶ አብዱልሐኪም እስማኤል



መሐመድ ኑር ሼክ

ፎቶ- ገባቦ ገብሬ

# የመስኖ ልማት -
## የሶማሌ ክልል አዲሱ የሥራ ባሕል

ኢያሱ መሰለ

መንግሥት ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ ራስን የመቻል እንዲሁም በከፍተኛ ወጪ ከውጭ የሚገባውን የምግብ ፍጆታ ለማስቀረት በያዘው አቅጣጫ አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ነው። በዚህም ከመኸርና ከበልግ እርሻ የሚገኘውን ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ በተጨማሪ እየተካሄደ ባለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሀገራዊ የስንዴ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር ስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የሰብል ልማቱ አርብቶ-አደሩ በብዛት በሚኖርባቸው ክልሎች ጭምር እየተስፋፋ ይገኛል። በእነዚህ ክልሎች የስንዴና የሩዝ እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በስፋት እየተሠራበት ሲሆን፣ ይህም የአርብቶ አደሮችን ሕይወት መቀየር የሚያስችል ተግባር እየሆነ መምጣት ጀምሯል።

ሕይወቱን በአርብቶ አደርነት እና በንግድ ሥራ የሚመራው የሶማሌ ክልል ሕዝብም የዚህ አንድ ማሳያ ሆኖ ይጠቀሳል። በክልሉ የመስኖ ልማትን አዲስ የሥራ ባሕል በማድረግ ትርጉም ያለው ሥራ እየተሠራ ነው።

ይህንን ሰሞኑን በክልሉ ተገኝተን ባደረግነው የመስክ ጉብኝት ተመልክተናል። በክልሉ ሸበሌ ዞን የምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ይገኛል። ከዞኑ 10 ወረዳዎች ሰባቱ ከዋቤ ሸበሌ ወንዝ ጋር ኩታ ገጠም ናቸው። ከሰባቱ ወረዳዎች መካከልም የበረሃኖ ወረዳ አንዷ ናት። ወረዳዋ ለግብርና ሥራ ምቹ የሆነ ሜዳማና ለም አፈር አላት። ለዘመናት አጠገቧ ከሚገማሸረው ዋቤ ሸበሌ ወንዝ ጋር ተኮራርፋ ነው የኖረችው ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን መንግሥት ለመስኖ ልማት የሰጠውን ትኩረት ተከትሎ የበረሃኖ ሜዳማና ለም መሬት ከዋቤ ሸበሌ ወንዝ ጋር ተስማምተው መኖር ጀምረዋል። ይህ ለጥ ያለና በዓይን ለማዳረስ የሚታክተው መሬት ዛሬ በልምላሜ ፈክቶ አዲስ የተፈጥሮ ገጽታን ተላብሷል። ከጓሮ አትክልት እስከ ተለያዩ አዝርዕቶች ይመረቱበታል።

ሌላው የሚገርመው ደግሞ ለመስኖ ልማት በተገነባው ቦይ ውስጥ የሚፈሰው ውሃ ብቻ አለመሆኑ ነው። ውሃውን ተከትሎ የሚመጣ ሌላም ሲሳይ አለ፤ ዓሣ። ይህ ዓሣ ለአካባቢው ሌላ በረከት ሆኗል። ዓሣው በተለይም በእርሻ ማሳው ላይ በጉልበት ሠራተኝነት ተቀጥረው ሕይወታቸውን ለሚመሩ ሰዎች የዕለት ተዕለት ምግባቸው መሆን ችሏል።

እነዚህ ሠራተኞች ብዙም ሳይደክሙና ሳይታክቱ እንደዋዛ መንጠቋቸውን ወርውረው ዓሣ ሲያወጡ ለተመለከተ ሕይወት በምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ምን ያህል ቀላል መሆን መጀመሯን መረዳት አይቸገርም። የሌማት ትሩፋት ትክክለኛ ትርጉምንም በተግባር ይረዳል።

አቶ አብዱልሐኪም እስማኤል በሶያል ኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተው በኢንቨስትመንት በወሰዱት 50 ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ ዘርተው ሲንከባከቡ ያገኘናቸው ባለሃብት ናቸው። በቀድሞው መንግሥት ይደረግባቸው በነበረው ጫና ምክንያት ኑሯቸውን በስደት አውሮፓ ውስጥ ያሳልፉ እንደነበር ይገልጻሉ።

ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በክልሉ የተገኘውን ሠላም እያጣጣሙ ሠርቶ የመኖር ተስፋ ሰንቀው በመስኖ ልማት ተሠማርተዋል። በአካባቢው በኢንቨስትመንት ከተረከቡት ሃምሳ ሄክታር እርሻ ግማሹ ላይ የዘሩት ሩዝ ቡቃያ ማሳውን አረንጓዴ ማልበስ ጀምሯል። የተቀረውንም ሄክታር ማሳ ለተመሳሳይ ዓላማ አዘጋጅተውታል።

አቶ አብዱላሂ የአካባቢው መስተዳድር ከዚህም በላይ ሰፊ መሬት ቢሰጣቸው የማልማት አቅም እንዳላቸው ይናገራሉ። በግብርናው ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ሲያስቡም ትርፍን ብቻ አስበው አይደለም። አርብቶ አደሩ ከእንስሳት እርባታ ውጭ ሌላም ሕይወቱን የሚመራበት ፀጋ እንዳለው ለማሳየትና አርዓያ ለመሆንም ጭምር እንደሆነ ይገልጻሉ።

በዋቤ በሸበሌ ወንዝ ዳርቻ ያሉ አርብቶ አደሮች ነገ ሶማሌ ክልልን በሩዝ ምርት ተጠቃሽ በሚያደርጉበት በዚህ ሥራ እርሳቸው ፋናወጊ መሆናቸው እንደሚያኮራቸውም ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሸበሌ ወንዝን ጠልፎ ለመስኖ ሥራ ዝግጁ ማድረጉ እሳቸው እና ሌሎች የክልሉ ነዋሪዎች በመስኖ ልማት እንዲሠማሩ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ፕሮጀክቱ የትራክተር፣ የምርጥ ዘር፣ የመድኃኒት አቅርቦት እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ አገልግሎት መስጠቱ ለሥራው የበለጠ ተነሳሽ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ከለውጡ ወዲህ ሶማሌ ክልል ሠላም ማግኘቷ እርሳቸውና መሰል ጓደኞቻቸው ከስደት ተመልሰው በልማት ሥራዎች ላይ እንዲሠማሩ አርጓቸዋል።

‹‹ሶማሌ ክልል በየትኛውም ዘመነ-መንግሥት ሠላም አግኝታ አታውቅም›› የሚሉት አቶ አብዱልሐኪም፤ ሠላም የምናቅደውን ሁሉ ሠርተን ውጤታማ ለመሆን፣ ከቦታ ቦታ በነፃነት ለመንቀሳቀስ፣ በአጠቃላይ ለሀገር ልማትና እድገት መሠረት እንደሆነ ያስረዳሉ። አሁን በሶማሌ ክልል የሰፈነው ሠላም የሶማሌ ሕዝብን በእጅጉ ጠቅሟል፤ መላው የሀገሪቱ ሕዝብ የሠላም ተጠቃሚ እንዲሆንም እያንዳንዱ ሰው ከመንግሥት ጎን መቆም ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹በክልሉ ሠላም በመስፈኑ በስደት እንኖር የነበርን የአካባቢው ተወላጆች ወደ ሀገራችን እየገባን በልማት ሥራ እንድንሳተፍ በር ከፍቶልናል፤ ሌሎችም እኛን ተመልክተው ወደ ሀገራቸው እየገቡ በልማት ሥራ ላይ እንደሚሳተፉ እጠብቃለሁ። እንዲህ አይነት ዘመን ያሳየኝን አላህን አመሰግናለሁ፤ መንግሥትም ለክልሉ ሠላም መጠበቅ ስላደረገው ሁሉ አመሰግናለሁ›› ይላሉ ፡፡

ሌላው በፕሮጀክቱ መሬት ወስዶ ሲሠራ ያገኘነው የአልኬሄራት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው። እርሱም ሩዝ በማልማት ላይ ይገኛል። የማኅበሩ ተወካይ ወጣት መሐመድ ኑር ሼክ እንደነገረን፤ ማኅበሩ ከፕሮጀክቱ ላይ 25 ሄክታር መሬት ተረክቦ የተለያዩ ሰብሎች እያመረተ ለገበያ ያቀርባል።

አሁን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ሩዝ ዘርቷል። ሩዝ ማምረት እንደሚቻል በምርምር ማዕከሉ ከተረጋገጠ በኋላ ማኅበሩ ሳያቅማማ በተሠጠው 25 ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ ዘርቷል። በአሁኑ ሰዓትም ሩዙ በቡቃያ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ሩዝ በሦስት ወር ውስጥ የሚደርስ ሰብል መሆኑን ጠቅሶ፣ ሰብሉ ሲደርስ ቶሎ ሰብስቦ ለሌላ ሥራ ለማዋልም ይጠቅማል ሲል ይገልጻል። በሶማሌ ክልል ሩዝን አዘውትሮ ለምግብነት መጠቀም የተለመደ ነው ያለው ወጣት መሐመድ፣ ወደፊት ሩዙን እዚሁ ማምረት ከተቻለ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ አውጥቶ ምርቱን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ይቀራል ብሏል። የአካባቢው አርሶ አደርም ቀስ በቀስ ሩዝ ማምረትን እየለመደ እንዲሄድ የሚያስችል መሆኑን ጠቁሟል።

ኢንጂነር አብዱዋሂድ ሙሂዲን የምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማናጀር እንዳስረዱት፤ መንግሥት ወረዳዋ ለመስኖ ልማት ያላትን ተመራጭነት በማጥናት ‹‹የምዕራብ ጎዴ የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን›› ገንብቶ እ.አ.አ በ2024 ለተጠቃሚዎች ክፍት አድርጓል። ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ ሰባት ሺ 600 ሄክታር ይሸፍናል፤ በአሁኑ ሰዓት ግን እየለማ ያለው ሁለት ሺ ሄክታር ብቻ ነው።

የመስኖ ፕሮጀክቱ ወደ አገልግሎት ከገባ ጊዜ ጀምሮ የበጋ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሰሊጥ ይለሙበታል፤ ሽንኩርት እንዲሁም ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግሉና የአርብቶ አደሩን ፍላጎት የሚያሟሉ የሣር አይነቶችም ተተክለውበታል።

በፕሮጀክቱ ድጋፍ ሰጪነትና በባለሃብቶች ተሳትፎ ለመጀመሪያ ጊዜ በ800 ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ የማምረት እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ ተገብቷል። ለዚህ ይረዳ ዘንድ አስቀድሞ ምርምሮች ተደርገው አበረታች ውጤቶች ታይቷል።

የጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ከክልሉ የግብርና ምርምር ማዕከል በሚደረግለት ድጋፍ በዚያው በፕሮጀክቱ ውስጥ የራሱን የምርምር ጣቢያ አቋቁሟል። ስለሆነም ውጤታማነቱ በሙከራ ሳይረጋገጥ የሚዘራ ወይም የሚተከል ነገር አይኖርም።

አብዛኛዎቹ የበርሃኖ ወረዳ ነዋሪዎች የአርብቶ አደርነት ሕይወትን የሚመሩ መሆናቸውን የጠቀሱት ኢንጂነር አብዱዋሂድ፣ የመስኖ ፕሮጀክት ሥራው ከጀመረ በኋላ ግን በቆሎ፣ ሰሊጥና ሽንኩርት እያመረቱ ከእርሻ ሕይወት ጋርም እየተለማመዱ መምጣታቸውን ይገልጻሉ። በቀጣይም የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ሩዝ የማምረት ልምድ እንዲያዳብሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ብለዋል።

የምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ለአካባቢው ነዋሪ እንደ ሽንኩርት እና ቲማቲም የመሳሰሉ ምርቶች ከኦሮሚያና ከደቡብ ክልሎች ይመጡለት እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን ግን በፕሮጀክቱ የሚመረቱ ምርቶችን እስከ አዲስ አበባ ድረስ ለገበያ በማቅረብ አዲስ ታሪክ እየተሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

በክልሉ እስከ ቀጣይ የመኸር ወቅት ድረስ በሦስት ሺ ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ የማምረት አቅድ እንደተያዘ የገለጹት ኢንጂነር አብዱዋሂድ፣ ከዚህ ውስጥ በበርሃኖ ወረዳ ብቻ 800 ሄክታር መሬት በሩዝ ለመሸፈን ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል። አሁን ላይ 400 ሄክታር፤ ከቀጣይ ሶስት ወር በኋላ ሌላ 400 ሄክታር መሬት በሩዝ ዘር ለመሸፈን ታስቧል ብለዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በምዕራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ250 ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ ተዘርቶ መብቀል ጀምሯል። ቀሪው 150 ሄክታር ደግሞ በወረዳው የተለያየ አካባቢ ባሉ አርሶ አደሮች እየተሸፈነ ይገኛል።

የመሬት አሰጣጥ ሥርዓቱን በተመለከተም በመስኖ ልማቱ መሥራት የሚፈልጉ አካላት መጀመሪያ ከተደራጁና የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው ከመጡ ባላቸው አቅም ልክ መሬት እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል። በቀጣይም ውጤታማነታቸው እየተለካ ተጨማሪ አቅርቦት ይደረግላቸዋል ብለዋል። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የሚፈልጉትን መሬት ለማግኘት መጀመሪያ በትንሽ መሬት ላይ ሠርቶ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ይህን አሠራር መከተል ያስፈለገበት ምክንያት መሬቱ ጦሙን እንዳያድር ስለሚፈለግ ነው።

ለግብርና ሥራው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማለትም ምርጥ ዘር፣ ትራክተር፣ ፀረ አረምና ፀረ ተባይ መድኃኒቶችን ከፕሮጀክቱ ያገኛሉ፤ ሙያዊ ድጋፍና ክትትልም ይደረግላቸዋል። ከእነርሱ የሚጠበቀው የሰው ኃይል አሟልቶ ወደ ሥራ መግባት ብቻ ይሆናል።

የመስኖ ልማቱ ለአካባቢው ማኅበረሰብ አዲስ የሥራ ባሕል ከመሆን አልፎ፤ በመስኖ ሥራ ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሃብቶችንም በሰፊው እየጋበዘ ይገኛል። ከእርሻ ዝግጅት እስከ ምርት መሰብሰብ ባለው የሥራ ሂደት ለክልሉና ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለመጡ በርካታ ሰዎችም የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።


የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሙስጠፌ መሐመድ የክልሉን የግብርና ሥራ አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በሦስት ሺ ሄክታር መሬት ላይ ሩዝ ለማምረት ወደ ሥራ ተገብቷል። በክልሉ ካሉት 11 ዞኖች ውስጥ ለሩዝ ምርት ተመራጭ ናቸው ተብለው የተለዩት የሸበሌ እና የሲቲ ዞኖች ናቸው። እነዚህ ዞኖች ከፍተኛ የውሃ አቅምና ለም መሬትን አስተሳስረው የያዙ መሆናቸውን ርዕሰ መስተዳድሩ ጠቅሰው፣ የሩዝ ምርትን ለማምረት አመቺነት እንዳላቸው አስታውቀዋል። አርብቶ አደሩ ከፊል አርሶ አደር በመሆን የአካባቢውን ፀጋዎች ተጠቅሞ በሚያመርተው ምርት በምግብ ራስን የመቻል መርሐ ግብሩ እውን ለማድረግ እየተጋ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ በቅርቡ ለጋዜጠኞች እንዳስታወቁት፤ እንደ ሀገርም በሩዝ ልማት ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው፤ አምና ከስምንት ሚሊዮን ኩንታል ያልበለጠ የሩዝም ምርት መገኘቱን አስታውሰው፣ ዘንድሮ 38 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል ብለዋል።

ማህበራዊ
# አስኳላ

# የትምህርት ስብራቱን በማያዳግም ርምጃ መጠገን

ግርማ መንግሥቴ



“የትምህርት ስብራት” የጋራ ቋንቋ ከሆነ ቆየ። በተለይ ከለውጡ በኋላ “የትምህርት ስብራት” የሚለው “ብሶት የወለደው“ ኃይለ-ቃል አየር ለአየር በመናኘት የሚዲያው ሁሉ፣ የአጀንዳዎች ሁሉ፤ የማኅበረሰቡ ውይይቶች ሁሉ የበላይ ርዕሰ ጉዳይ በመሆን እነሆ እስካሁንም አለ።

ቀደም ሲል ተግባር ላይ ውሎ በነበረው “አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ“ ምክንያት በትምህርቱ ዘርፍ ያልደረሰ የትምህርት ስብራት የለም። ይህም ዛሬ ለውጥን ተከትሎ የመጣ ሳይሆን አጠቃላይ ሕዝቡ ቅሬታ ሲያቀርብበት የነበረ፤ እስከ “ዮዲት ጉዲት“ ድረስ የዘለቀ ወቀሳ ሲሰነዝርበት የቆየ አንገብጋቢ ጉዳይ እንደ ነበር የሚታወስ ነው።

የዚህ ጽሑፍ መነሻ በቅርቡ (አዲስ ዘመን፣ ግንቦት 26 ቀን 2016 ዓ.ም) የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል (ዶ/ር) ከጋዜጣው ጋር ቆይታ ባደረጉበት ወቅት ‹‹የትምህርት ስብራትን ለመጠገን የሁሉም አካላት ትኩረትና ርብርብ ያስፈልጋል›› በማለት የተናገሩት ሲሆን፤ ይህ የእሳቸው የቅርብ በመሆኑ ጠቀስነው እንጂ እስከዛሬ ድረስ ስለ “የትምህርት ስብራት?” ያልተባለ የለም። ያልተባለ አይኑር እንጂ በደፈናው ስለ መሰበርና መሰባበሩ ከመናገር ያለፈ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ . . . በማለት ቆጥሮ የተናገረ የለም። ወይም፣ ሀ፣ ለ፣ ሐ . . . በማለት ዘርዝሮ ያስቀመጠ አልተገኘም። በመሆኑም ጉዳዩ ከ”ሾላ በድፍን” ይወጣ ዘንድ ይህ ጽሑፍ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ ከ1ኛ ደረጃው እንጀምር።

የትምህርት ፖሊሲው ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ድረስ አንድ መምህር ያስተምር (”ሰልፍ ኮንቴይንድ” ይባል የነበረው የማስተማር ሥነ-ዘዴ) ተብሎ የተወሰነ ጊዜ “ኧረ በሕግ“ ቢልም የሰማው አልነበረም። በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪና አስተማሪው ቦታ ሲለዋወጡ “ኧረ ይሄ ነገር አያዋጣም“ ሲባል፣ በወቅቱ የነበረው መልስ “ንክች ያባ ቢላዎ ልጅ“ ነበር። “ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ያለ ምንም አይነት ፈተና (ምዘና) ይለፉ“ የተባለ ጊዜ “እንዴ፣ እንዴት እንዴት ነው ነገሩ . . .“ በማለት ያላጉረመረመ ሰው ካለ እሱ እዚህ አገር ያልነበረ ነው። ምኑ ቅጡ - ከለውጡ በፊት በነበሩት ዓመታት በትምህርት ላይ የደረሰው ስብራት፣ ቅጭትና አጠቃላይ ኪሳራ እዚህ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

ስብራት፣ ቅጭትና ኪሳራው ከታችም አልፎ ወሳኝ የሆኑትን መምህራንን ሳይቀር የጎነተለ ሲሆን፤ በጽሕፈት ቤታቸው ተገኝተን ያነጋገርናቸው፣ በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን እና የትምህርት ልማት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገደች ምሬሳ እንደሚሉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ (በተለይ ለመምህራን) የክረምት ኮርሶች ሁሉ ሳይቀሩ በችግር የተተበተቡና በዚሁ በተበተባቸው ችግር ምክንያት ለውጡን ተከትሎ እንዲቋረጡ ተደርገዋል።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ፣ በሀገራችን ከሚገኙት 800ሺህ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች (የመንግሥት) ከ94 በመቶ በላይ የሆኑት ተገቢው የትምህርት ደረጃ (ማስረጃ) ያላቸውና የሚሠሩበትን የሥራ ዘርፍ የሚመጥን ነው። ይሁን እንጂ ብቃትን ለማረጋገጥ በተደረገ የዳሰሳ ጥናትም ሆነ የተገኘው የተማሪዎች የፈተና ውጤት (በተለይ ባለፈው ዓመት የተመዘገበው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት) የሚያሳየው መምህራን በሙያው የሚፈለገውን የትምህርት ደረጃና ማስረጃ ይያዙ እንጂ የአቅም ክፍተት ያለባቸው መሆኑ ነው።

የዴስክ ኃላፊዋ እንደነገሩን ከሆነ፣ በየዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በክረምት ኮርስ (ሰመር ፕሮግራም) ሲከታተሉ የነበሩ ሠልጣኝ መምህራን እንዲያቋርጡ የተደረጉት በመምህራን ልማት ስም ሲካሄድ የነበረው ፕሮግራም “የአመራር ክፍተት የታየበት፣ ወጥነት የሌለው፣ ግማሹ በሁለት ወር፣ ግማሹ በሁለት ዓመት፤ ያሰኘው ደግሞ ባሰኘው ጊዜ የሚያስመርቅበት፤ የተዘበራረቀና መምህራን ተመልሰው የትምህርት ጥራትን ሊያመጡ በሚችሉበት አይነት ዝግጅት አልነበረም እየተካሄደ የነበረው። በመሆኑም፣ ጥናት ተደርጎ በጥናቱ ግኝት መሠረት ለጊዜው እንዲቆም ተደርጓል፤ በፕሮግራሙ 8ሺህ አካባቢ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢኤ) እና 34ሺህ አካባቢ ሁለተኛ ዲግሪ (ኤምኤ) መርሐ ግብሮችን የሚከታተሉ መምህራን ነበሩ። አካሄዱ የተሳሳተ ነገር ስላለው ተቋርጧል።“ ይህም ሌላው የትምህርት ዘርፉ ከወለምታም የዘለለ፣ ቅጭትና ስብራት ስለ መሆኑ ከበቂ በላይ ማስረጃ ነውና ስብራቱን “የቱ ጋ?” በማለት ለሚጠይቁ ወገኖች መልስ ይሆናል።

የነበረው የተሳሳተ የትምህርት ፖሊሲ በትምህርቱ ሴክተር ያላደረሰው ስብራት የለም የሚሉ የትምህርቱ ዘርፍ ተቆርቋሪዎች 2ኛ እና 3ኛ ክፍል ተማሪዎች ማንበብና መጻፍ አይችሉም፤ ከአጠቃላይ የማትሪክ ተፈታኞች 3 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው ከ50 በመቶ በላይ በማምጣት ለአቅመ ከፍተኛ ትምህርት የደረሱት እና ለመሳሰሉት “የሚጠበቅ“ ከሚል መልስ በዘለለ ምንም ትኩረት ሳይሰጡ፤ ከፍተኛ ትኩረታቸውን የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ በመሸመት በየቢሮው የተሰገሰገውና ዜጋን በሚያተራምሰው፤ ዲግሪን እንደ አልባሌ ወረቀት በሚቸበችበው ላይ በማድረግ ያንን “አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ“ ሲወቅሱና ሲያወግዙ ይታዩና ይሰማሉ። ይህም ሌላው የነበረው የትምህርት ሥርዓት ስብራት መሆኑን ያሰምሩበታል። “ያለፈው ይበቃል” በሚል ዘይቤ ድርጊቱ መቸም መቸም እንዳይደገምም ይማፀናሉ።

የነበረውን የ12ኛ ክፍል ማትሪክ መውሰጃ ወደ 10ኛ ዝቅ በማድረግ ሁሉንም ነገር አብሮ ዝቅ ያደረገው የትምህርት ፖሊሲ፣ የነበረውን የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች አራት ዓመት ዝቅተኛ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ ወደ ሦስት ዓመት በማውረድ ሁሉም ነገር አብሮ እንዲወርድ፤ የሁሉም ነገር አይንና ጆሮ እንዲጠፋ ያደረገው የትምህርት ፖሊሲ በአገርና ትውልድ ላይ ያላደረሰው ስብራት ብቻ ሳይሆን፤ ያልሰረቀው የትውልድ እድሜና ሥነልቦና፣ ያልቀረጠፈው የአገር ኢኮኖሚ፣ ያላባከነው ጊዜና ጉልበት አልነበረም። በመሆኑም፣ አሁን እየተሠሩ ባሉ የለውጥ ሥራዎች ውስጥ ሁሉ ይህ ሁሉ ብክነት ታሳቢ ሊደረግና (“ነቨር ነቨር አጌይን” እንደ ተባለው) ዳግም እንዳይደገም ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ሳይቀሩ የክብር ዶክትሬት ማዕረግን በአካባቢ፣ በአምቻና ጋብቻ በመስጠታቸው ምክንያት ትምህርት ሚኒስቴር ከእንግዲህ እንዳይሰጥ ማገዱ (የአሰጣጥ መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል) የዚሁ ውድቀታችን፣ የትምህርት ስብራታችን አንዱና ሌላው አስቂኝ ማሳያ ነው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በከፋ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው መገኘታቸውም እንደዛው።

ከላይ እንደ ጠቀስናቸው፣ እንደ የኮተቤ ሜትሮ ፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል (ዶ/ር) ሙያዊ አስተያየት ከሆነ የትምህርት ስብራት የተጀመረው የቀድሞውን የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በካልቾ ከመምታትና ብቁ መምህራንን ከማሠልጠን አኳያ ሲወጣ ከነበረው ተልዕኮና ኃላፊነት መንቀል የተጀመረ ጊዜ ነው።

ፕሬዚዳንቱ እንደ ተናገሩት ከሆነ በ1935 ዓ.ም የመጀመሪያው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሆኖ መደበኛ ትምህርት ማስተማር የጀመረውን ተቋም፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የትምህርት ዓይን ከፋች የሆነውን ተቋም፤ እንደነ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ከበደ ሚካኤልን የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች የተማሩበት የመደበኛ ትምህርት ዓይን ከፋች የሆነውን የእውቀት ደብር፤ ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ መምህራን ኮሌጅ ሆኖ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መምህራንን ለኢትዮጵያ ያበረከተ አንቱ ሊባል የሚገባውን ትልቅ ተቋም፤ አንጋፋ፣ ብዙዎችን ያፈራና በብዙኃኑ ሕዝብ ላይ ዐሻራውን ያሳረፈን ተቋም ወገቡን መምታት ሳያስፈልግ መመታቱ በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖውን ኣሳርፏል። ዶክተሩ ምክንያቱ ሲገልፁም “እንደስሙ ሳያድግ የቆየበት ምክንያት የነበሩት ሥርዓተ መንግሥታት ባሳረፉበት ጫና ነው። ሰውና ተቋምን ለይቶ ባለማየት በሰዎች ላይ ባላቸው ግላዊ ግጭትና ጥላቻ ተቋሙ ወደ ኋላ እንዲቀር ተደርጓል።“ ይህም በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ደርሶ የነበረ አንዱ ስብራት ነውና አሁንም እየተሠሩ ያሉ የለውጥ ሥራዎች ይህንን አይነቱን በተቋም ላይ ሳይቀር ያተኮሩ ስህተቶች እንዳይፈፀሙና ሀገርና ሕዝብን ዳግም ዋጋ እንዳያስከፍሉ ጥንቃቄ ያሻል።

“ለረጅም ዓመታት በትምህርት ዘርፉ አገልግለዋል። አሁንም በሀገሪቱ የመጀመሪያና ብቸኛ የሆነውን የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ይመራሉ። በእርስዎ እይታ የኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ ዋነኛ ችግር ምንድን ነው?” ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ፡-

የኢትዮጵያ ትምህርት ዋንኛ ችግሮች ሁለት ጉዳዮች ናቸው። የመጀመሪያው ችግር ባለፉት ዓመታት ችግሮችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ከመፍታት ይልቅ በጨበጣ ለመፍታት ሲደረግ የነበረው ጥረት ነው። ችግሩን በጥናት ለይቶና መፍትሔዎችን አስቀምጦ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ችግርን በስብሰባ ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ይስተዋል ነበር። ሁለተኛው ችግር ደግሞ ጥናት ተብለው የሚቀርቡ ጥናቶችም በረጂ ድርጅቶች ላይ የተንጠለጠሉ መሆናቸው ነው። ጥናቱ በርዳታ ላይ የተንጠለጠለ ስለሆነ የሆነ ሀገር የተሠራውን ጥናት አምጥተው የስም ለውጥ ብቻ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ የተጠና አስመስለው ያቀርቡ ነበር። እነዚህ ጥናቶች በርካታ የሀገር ሀብት ቢፈስባቸውም መሠረታዊ ችግሩን የለዩ ባለመሆናቸው ሊፈቱት አልቻሉም።

ትምህርት ተሰብሮ ብልጽግና አይረጋገጥም፤ ትምህርት ተሰብሮ ልማት ሊለማ ይችላል ግን ያልተማሩ ሰዎች መጥተው ያፈርሱታል። ልማታችን ሰው ተኮር ካልሆነ ከባድ ነው። መሰል ችግሮችን ለማስቀረት በማሰብ ከተሠሩት ሥራዎች አንዱ በሀገራችን ምሑራን የተዘጋጀ ሀገር በቀል ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ነው። በዚህም የእኛን ችግር ማዕከል ያደረገና ራዕያችንን የሰነቀ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅተናል።

> ትምህርት ተሰብሮ
> ብልጽግና አይረጋገጥም፤
> ትምህርት ተሰብሮ
> ልማት ሊለማ ይችላል ግን
> ያልተማሩ ሰዎች መጥተው
> ያፈርሱታል። ልማታችን
> ሰው ተኮር ካልሆነ ከባድ
> ነው

በማለት መመለሳቸው አስተማሪነቱ እንዳለ ሆኖ፤ የአሁኑ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ብርሀኑ ነጋ ደግሞ አሁን ላይ በትምህርቱ ዘርፍ እየታየ ያለው ስብራት ለውጥ ከመምጣቱ በፊት በነበሩት “27 ዓመታት በትምህርቱ ላይ ሆን ተብሎ በተሠራ አሻጥር“ ምክንያት ነው። (“አሻጥር“ የሚለው “ሳቦታዥ“ የሚለውን እንግሊዝኛ ቃል የሚወክል ከመሆኑ አኳያ በቀላሉ ሊታይ የሚችል ጽንሰ ሀሳብ አይደለም የሚሉ ብዙዎች ሲሆኑ፤ ጉዳዩ የሚያወያይ፣ የሚያመራምር ወዘተ ስለ መሆኑ በስምምነት የሚያልፉ በርካቶች ናቸው።) ብርሃነመስቀል (ዶ/ር) መፍትሔ በማለት ያስቀመጡትና:-

ችግሩ ሰፊ ስለሆነ በቀላሉ ለመውጣት ሊከብደን ይችላል። ግን ያሉ ሀገራዊ አቅሞቻችንን አስተባብረን ከተጠቀምን ለውጥ የማናመጣበት ምክንያት አይኖርም። ችግሩ የመንግሥትን ትኩረትና የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይፈልጋል። ለኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲም መንግሥት ሙሉ ትኩረት መስጠትና ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች እንዲሟሉ ከማድረግ አንጻር እንዲያግዘን እንፈልጋለን። ዩኒቨርሲቲውም ዘር ላይ የሚስተዋለውን ችግር ከመቅረፍ አንጻር የበኩሉን ሚና ለመወጣት በቁርጠኝነት የምንሠራ ይሆናል። ሕዝቡ ደግሞ በየአካባቢው ልጆቹን ለማስተማር የሚሄዱለትን መምህራን ማክበርና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ከዚህ ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገው የነበሩት፣ በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን እና የትምህርት ልማት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገደች “ትምህርት ማኅበራዊ ጉዳይ ነው። ባለቤቱም ማኅበረሰቡ ነው። በመሆኑም ለትምህርት ጥራት መጠበቅም ሆነ አለመጠበቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁሉም ኃላፊነት አለበት። በተለይ ባለ ድርሻ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች ቀጥተኛ ተሳታፊዎች በመሆናቸው እየተከናወነ ካለው የትምህርት ሥርዓት ለውጡ ጎን ሊቆሙ ይገባል። በትምህርት ላይ የሚሠሩ ተቋማትም ከእኛ (ትምህርት ሚኒስቴር) ያልተናነሰ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ አብረን በጋራ ልንሠራ ይገባል” እንዳሉት ሁሉ፤ እኛም የእነዚህኑ ባለሙያዎች አስተያየት በማፅደቅ ዝግጅታችንን በዚሁ እንቋጫለን።

# ወቅታዊ

# “ሐረር ዳግም እየተወለደች ነው”

- አቶ ኦርዲን በድሪ
- የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር


ፎቶ፦ አሸናፊ ጉደታ

ሙሉቀን ታደገ

**የሠላም ከተማዋን ሐረር በጉያው አቅፎ በያዘው የሐረሪ ክልል የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ነው። ክልሉ በልማትም ሆነ በመልካም አስተዳደር ዘርፍ እመርታን እያሳየ ከመሆኑም ባሻገር ታሪካዊቷን ሐረር ከተማ በቱሪስቶች ተመራጭ ለማድረግም የሚሠሩ ሥራዎችም ዓይነ ግቡ ናቸው፡፡**

**የፍቅር እና የአብሮነት ከተማ የሆነችውም ሐረርም ከ1ሺ ዓመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረች ቢሆንም የእድሜዋን ያህል ሳታድግ ዘመናትን ተሻግራለች። ዛሬ ግን በመሠረተ ልማት ዘርፍ እና ተያያዥ ልማቶች እያሳየችው ያለው እመርታ ከተማዋ ዳግም የተወለደች ያህል የሚያስቆጥር ነው። ይህንንም በክልሉ የሥራ ስምሪት አድርጎ የነበረው የጋዜጠኞች ቡድን ተዘዋውሮ ልማቱን ለመመልከት ችሏል፡፡**

**በተለይ ከሰውጡ ወዲህ የተሠሩ ሥራዎችን በተመለከተ በክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦድሪን በድሪ መሪነት የጋዜጠኞች ቡድን ልማቱን ተዘዋውሮ ለመመልከት ችሏል።**

**በአጠቃላይ በአዲስ ጎዳና የሚገኘው የሐረሪ ክልል ከለውጡ በኋላ ባስመዘገባቸው ውጤቶችና ቀጣይ ሥራዎች ዙሪያ ከርዕሰ መስተዳድሩ ጋር የተደረገው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል፤ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በሐረሪ ክልል የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦች መገለጫ የሆኑ ሙዚየሞች ተገንብተዋል፤ በመገንባት ሳይ ያሉም አሉ። እነኝህ ሙዚየሞች የሐረርን የሠላም ከተማነት እሴት ከማጉላት አንጻር የሚኖራቸውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ኦርዲን በድሪ፡-** እንደመንግሥት ከልላችንን ብሎም ሀገራችንን ወደተሻለ የእድገት ደረጃ ከፍ ለማድረግ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ሥራዎችን እያከናወንን ነው። ከዚህ አኳያ በኢኮኖሚው ዘርፍ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን የበለጠ በማጠናከር የሀገራችንን ብልጽግና እውን ለማድረግ እየሠራን እንገኛለን። በማኅበራዊ ዘርፉም በጥናት ላይ ተመርኩዘን የክልሉን ማኅበራዊ የልማት ሥራዎች ለማጠናከር በርካታ ሥራዎችን እያከናወንን ነው።

በክልላችን ቋሚ ሀብት እንዲፈራ ወይም እንዲፈጠር ለማድረግ ከምንግዜውም በላይ ጠንክረን እየሠራን ነው። ይህን ለማድረግ በተለይ በመንግሥት በጀት የሚሠሩ የጀመርናቸው የለውጥ ሥራዎች አሉ። አንዱ የለውጥ አቅጣጫ የመንግሥትን በጀት ቋሚ ሀብትን ለማፍራት በሚያስችል መልኩ ሥራ ላይ ማዋል ነው። ይህን እውን እንዲሆን ከዘንድሮ አጠቃላይ የመንግሥት በጀት 58 በመቶውን ለካፒታል በጀት መድበናል። 42 በመቶውን ብቻ ለሥራ ማስኬጃ እና ለደሞዝ ተጠቅመናል።

58 በመቶው የመንግሥት በጀት ቋሚ ሀብት መፍጠር ለሚያስችሉ ለመንገድ ሥራ፣ ለውሃ፣ ለመብራት እና ለሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች እንዲውሉ እያደረግን ነው። ይህ በጀት ለማኅበራዊ ሥራዎች ማለትም ለትምህርት ቤቶች፣ ለጤና ተቋማት ግንባታዎች እና ለመሳሰሉት ቋሚ ሀብቶች ግንባታም የሚውል ነው።

ይህ አይነት አሠራር ቋሚ ሀብትን በማፍራት ለነገው ትውልድ የተሻለ ሕይወት ከመፍጠር አኳያ በጣም ጠቃሚ እና ተመራጭ ነው። ቀጣዩ ትውልድ መሠረታዊ ፍላጎቶች የተሟሉ እንዲሆኑ ለማስቻል ዛሬ ያለን ሀብት ለዛሬ ሳይሆን ለነገ ትውልድ የሚለውን አሠራር እንደመርሕ ወስደን እየሠራን ነው። በቀጣይም አሁን የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በማኅበራዊ ዘርፉ በተለይም ከባሕል እሴት ግንባታ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወንን ነው። እንደሚታወቀው ከባሕል ጋር ተያይዞ የነበረው እይታ የነጠላ ትርክት እይታ ነበር። ታሪካችንም የነጠላ ትርክትን መነሻ ያደረገ ነበር። ይህ ደግሞ ለአብሮነት፣ ለአንድነት እና ለትብብር የማያመች እና ለተለያዩ ችግሮች እንድንጋለጥ የሚያደርግ ነው።

ያለፈው አካሄድ የእኔ ብቻ ባሕል ተብሎ ለልዩነት እና ለመከፋፋል መነሻ የሚሆን ትርክትን የፈጠረ ስለነበር ከዚያ ትርክት እና ከዚያ እሳቤ ለመውጣት እንደ ክልል ጥረት አድርገናል። አሁን ላይ ከነጠላ ትርክት እና ከነጠላ እይታ ወጥተን ወደ ወል ትርክት እና ወደ ወል እይታ እየገባን ነው። የጋራ የሚያደርጉ እና የሚያስተሳስሩ ባሕሎች የበለጠ ለማጎልበት ልንሠራ ይገባል፡፡

ይህን መነሻ ባደረገ መልኩ የሌሎች ክልሎችን የባሕል ማዕከል እና የእንግዳ ማረፊያ በክልላችን እየገነባን ነው። ባለፉት ሁለት ሦስት ዓመታት በክልላችን በተለያዩ ቦታዎች የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች ባሕል ሊያሳዩ የሚችሉ የባሕል እቃዎችን፣ አልባሳትን እና በሙዚየሞችን የማደራጀት ሥራዎች ሠርተናል። ከዚያ ባለፈ በተቻለ መጠን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የባሕል ቤቶች እንዲገነቡ አድርገናል። አሁን ላይ የሐረሪ እና የኦሮሞ የባሕል ማዕከላት ተገንብተው ሥራ ላይ ሲሆኑ የአፋር እና የሶማሌ ክልሎች ደግሞ የባሕል ማዕከሎቻቸውን ለመገንባት በሂደት ላይ ናቸው።

የሌሎችን ብሔር እና ብሔረሰቦች የባሕል ማዕከል በክልላችን ለመገንባት ለምን አስፈለገ? ከተባለ ምክንያቱም አብሮነትን፣ ወንድማማችነትን፣ እህትማማችነትን ለማጠናከር ጠቃሚ በመሆኑ ነው። የአብሮነት፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነት እና እህትማማችነት እሳቤ መጎልበት ደግሞ ለዘላቂ ሠላም በጣም አስፈላጊ ነው።

በነገራችን ላይ እንደዚህ አይነት የመተባበር እና መደጋገፍ እሴት ለሐረር ሕዝብ የመጀመሪያው አይደለም። ሐረር የሠላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነት እና የመቻቻል ከተማ ናት። ይህን ደግሞ እንዳይሸረሸር የመጠብቅ እና የበለጠ ጎልቶ እንዲታይ የማድረግ ሥራዎችን ደግሞ አሁን ጀምረናል።

አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ማድረጋችን እኛን በጣም ጠቅሞናል። ትልቁ የፈጠረልን ጥቅም ምንድን ነው? ከተባለ፤ ቀደም ብሎ ሐረር የምትታወቅበትን፤ ሁላችንም በጋራ አብረን የምንኖርባት፣ የምንለማባት፣ የምናድግባት የሠላም ከተማ ናት የሚለውን እሳቤ በእጅጉ ማጎልበት የቻለ ነው። ባሕልን ለሠላም፤ ባሕልን ለአብሮነት፣ ባሕልን ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት ከመጠቀም አኳያ ጥሩ ተሞክሮ የሚሆን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የጀጎል ግንብን መልሶ ማልማት አንድ ትልቅ ከተማ ማልማት ነውና የመልሶ ማልማት ሀሳቡ እንዴት መጣ? ወጪውን እንዴት መሸፈን ተቻለ? እድሳቱ ለቱሪስት ፍሰቱ የሚኖረውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ኦርዲን፡-** እንደሚታወቀው የሐረር ጀጎል በዩኔስኮ የተመዘገበ የዓለም አቀፍ ቅርስ ነው። ጀጎል ሲባል አጥሩ ብቻ አይደለም። በአጥሩ ውስጥ የሚኖሩ ቤቶችን፣ በቤቶች ውስጥ ያሉ ያኗኗር ዘይቤዎችን እና ባሕሎች እንዲሁም የሰዎች መስተጋብር ሁሉ እንደ ጀጎል ይታሰባል። የጀጎል ቅርስነትም ይህን ሁሉ የያዘ ነው።

ጀጎልን መልሶ ለማልማት በርካታ መነሻ ምክንያቶች አሉ። ጀጎል ከአንድ ሺህ አመት በላይ ታሪክ ያለው ነው። በጊዜ ሂደት የተነሳ በተለይም ከ20 ዓመት በፊት በነበረው ሁኔታ ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቆ ነበር። ቅርሱም ከፍተኛ ስጋት ተጋርጦበት ነበር። ይህ በቅርሱ ላይ የተደቀነው የመበላሸት ስጋት ደግሞ በእኛ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሮብናል። ቅድመ አያቶቻችን ይህን ቅርስ ሠርተዋል ለዛሬው ትውልድ አበርክተዋል። ጀጎል ላይ የተፈጠረው ስጋት በእኛ ዘመን መፈጠር የለበትም የሚል ውይይት አደረግን፤ በውይይቱም ሀሳቦች ጎልብተው ወጡ። እኛ ያንን የመሰለ ቅርስ መሥራት ባንችል ለምንድን ነው መንከባከብ እና መጠበቅ ያቃተን? የሚል ከፍተኛ ቁጭት ተፈጠረ። ይህ ቅርሱን ለማደስ አንዱ መነሻ ወይም ገፊ ምክንያት ነው።

ስለዚህ ጀጎልን መጠበቅ እና መንከባከብ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ሲባል አንድ አካል ብቻውን የሚሠራው ሳይሆን ሁሉም ሰው በቻለው ልክ መሆን አለበት። ከዚህ አንጻር ጀጎልን እንደገና በማልማቱ ሂደት ሁሉም የማኅበረሰባችን ክፍል የተሳተፈበት ነበር። በመልሶ ማልማቱ የተገኘው ስኬት የጋራ ስኬት ነው።

ይህን ሥራ ለመጀመር እንደአመራር ማን ይሥራው? እንዴት ይሠራ? እና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ ከፍተኛ ውይይቶችን አድርገናል። ይህን ለማድረግ መጀመሪያ የጋራ መግባባት ላይ ደረስን። ቀጥሎም አመራሩ ይህን ለማድረግ ቁርጠኝነት ነበረው። በዚህም ቀድሞ የነበረውን ስጋት መቀነስ ብቻ ሳይሆን የተሻለ ሥራ መሥራት እንድንችል አድርጎናል።

ከእድሳቱ በፊት በጀጎል እና ዙሪያው ከፍተኛ የሆነ የፅዳት ችግር ነበር። በርካታ ሕገ ወጥ ተግባራት ይፈጸም ነበር። ለቱሪስትም ፈጽሞ ምቹ አልነበረም። ለነዋሪዎቹም በጣም አስቸጋሪ ነበር። አንዳንድ አካባቢዎች አይደለም ለመቀመጥ እና ለማለፍ እንኳን አስቸጋሪ ነበር።

አሁን ላይ ግን ጀጎልን ስንመለከት ሁሉም ነገሩ ተለውጧል። ለማመን የሚከብድ መሻሻሎች ታይተውበታል። አስደማሚ እና በአድናቆት እጅን በጉንጭ የሚያስጭኑ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ይህን የመሰለ ዕፁብ ድንቅ ሥራ ስንሠራ ምንም አይነት ገንዘብ ከመንግሥት በጀት አልተጠቀምንም። እያንዳንዱ ተቋም ከተመደበለት መደበኛ በጀት ቀንሶ እንዲሠራ ነው ያደረግነው። የክልላችን ዲያስፖራዎች ጨምሮ በሀገር ውስጥ ያለው ማኅበረሰባችን በስፋት ተሳትፎበታል። ወጪ ቆጣቢ በሆነ አካሄድ የጀጎል ገጽታ መመለስ ያስቻለ ሥራ ማከናወን ችለናል።

አሁን ላይ ጀጎል ከተደቀነበት ስጋት ወጥቶ ዙሪያው አልምተን አረንጓዴ አድርገነዋል። የቱሪስት ፍሰቱም ከዚህ ቀደም ከነበረበት ድባቴ ወጥቶ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል።

**አዲስ ዘመን ፡- ከማኅበረሰቡ አኗኗር ዘይቤ አኳያ ቤቶችን እንዴት አጣጥሞ ማደስ ተቻለ?**

**አቶ ኦርዲን፡-** ብዙ ከተሞች የራሳቸው ባሕሪ አላቸው። በአውሮፓ እና በእስያ ላይ የከተሞች ትልቁ ፈተና ቅርስ ይዘቱ ሳይለቅ በመጠበቅ እና በመንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ እንዴት ማስተላለፍ ይቻላል የሚለው ነው። በሌላ በኩል የነዋሪዎችን የመዘመን ፍላጎት ግምት ውስጥ አስገብቶ ቅርሶችን ማደስ ሌላኛው ፈተና ነው።

ዘላቂነት ያለው ሥራ ለማከናወን ሁለቱን አጣጥሞ እና ሚዛኑን ጠብቆ መሥራት ያስፈልጋል። ማኅበረሰቡ ሰማይ ጠቀስ ሕንጻ ይፈልጋል። ቅርስ እንጠብቅ ሲባል ደግሞ ይህን ማድረግ አይቻልም። ማኅበረሰቡ በጣም ዘመናዊ የሆኑ መንገዶችን ይፈልጋል። ቅርስ ሲኖር ደግሞ ይህን ማድረግ ከባድ ነው። ስለሆነም ከተማን ለማደስ የማኅበረሰቡን የመዘመን ፍላጎት እና የቅርሱን ይዘት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ገብተን ነበር።

በጀጎል ውስጥ ማኅበረሰቡ የማይኖር ከሆነ ቅርሱ ትርጉም የለውም። ሐረር ጀጎል ሕያዊቷ ሙዚየም (THE LIVING MUSEUM) የሚለውን እና የእኛን ዐቢይ መለያ ወይም ብራንድ ቦታ ያሳጣዋል። ስለዚህ ማኅበረሰቡ በጀጎል ውስጥ መኖር አለበት። በዚያ ለሚኖረው የማኅበረሰቡ ደግሞ መሠረታዊ ፍላጎቶችም ሊሟሉለት ይገባል።

አሁን የተሠራው የመልሶ ማልማት ሥራ ከዚህ በፊት ከጀጎል የወጣውን ማኅበረሰብ ይመልሳል የሚል እሳቤ አለን። ከእድሳቱ በፊት አካባቢው በጣም የቆሸሸ እና ለኑሮ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## “ሐረር ዳግም...

ከገጽ 9 የዞረ

የሚመች ስላልነበር ሰዎች በጀጎል መኖር አይፈልጉም ነበር። አሁን ግን በጣም ምቹ ሆኗል። በመሆኑም ቢያንስ እዚያ ያለው ሰው እዚያው ይቆያል የሚል ግምት አለን ።

**አዲስ ዘመን ፡- የጀጎልን እድሳት ጨምሮ በሐረር ከተማ እየተከናወኑ ባሉት የኮሪደር ልማቶች ሐረርን እንደገና ተወለደችም/ ተሞሸረችም የሚሉ አሉ። እርስዎ በየትኛው ይስማማሉ?**

**አቶ ኦርዲን፡-** ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የነበረን ሁኔታ ስንመለከት ሐረር የሥልጣኔ ማዕከል ነበረች። ጀጎል ላይ አሁን የምናያቸው አስደማሚ ቤቶች፣ መንገዶች እና አጥሮች በአብዛኛው ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የተሠሩ ናቸው። የቤቶቹ አሠራር፤ በግንቡ ውስጥ ያሉ ቤቶች ይዘት ስትመለከት በዚያ ጊዜ የነበረውን ሥልጣኔ ለማድነቅ ትገደዳለህ። የአጥሮቹ አቀማመጥ፣ ኪነ ሕንጻው እና የመሬት አጠቃቀም ስትመለከት እጅግ ማራኪ ናቸው ።

ሐረር በሥልጣኔው ቀዳሚ ነበረች። ለበርካታ ዓመታት ሐረር የምሥራቅ አፍሪካ የንግድ ማዕከልም ነበረች። የዓለም አቀፍ ንግድ ተካሂደውባታል። የራሷ የሆነ የመገበያያ ሳንቲሞች ወይም ገንዘብ ነበሯት። በኢትዮጵያ የራሳቸው መገበያያ ሳንቲም የነበራቸው አክሱም እና ሐረር ብቻ ነበሩ።

ነገር ግን በጊዜ ሂደት ሐረር የነበራትን ታላቅነት በተለያዩ ምክንያቶች እያጣች ሄዳለች። አሁን ደግሞ እንደገና እሱን የማደስ ሥራ ጀምረናል ። አሁን ላይ ጊዜው ለሐረር ህዳሴዋ ነው ብዬ አስባለሁ። ሐረር ዳግም እየተወለደች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሐረር ሆስፒታል ጥንታዊ ሆስፒታል ነው። በቀደመው ጊዜ የውጭ ሀገራት ዜጎች ጭምር የሕክምና አገልግሎት ያገኙበት የነበረ ነው። አሁን ላይ እየተከናወነ ያለው የጤና ዘርፍ ልማት ሜዲካል ቱሪዝምን ከማሳደግ አንጻር የሚኖረውን አስተዋፅዖ እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ኦርዲን፡-** በሐረር ረጅም ዓመታት የቆዩ፤ በሀገራችንም ቀደምት እና አንጋፋ የሚባሉት ብዙ ተቋማት አሉ። ከእነዚህ መካከል የሐረር ሆስፒታሎች፣ እድሜ ጠገብ ትምህርት ቤቶች፣ ፖስታ ቤት እና የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሽ ናቸው። አሁን እየተከናወነ ያለው “ከአጅፕ እስከ ደከር” ያለው የኮሪደር ልማት ሐሳቡ የመጣው እና የተጀመረው ባለፈው ዓመት ነው። ይህ ፕሮጀክት “የስማርት ሲቲ” መገለጫዎችን መነሻ ያደረገ ነው። መንገዶቹ 30 ሜትር ስፋት ያላቸው ናቸው ። የሳይክል እና የእግረኛ መንግድ አጣምረው ይዘዋል። “ስማርት ሲቲ” ሲባል በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ሊያሳልጥ የሚችል ማለት ነው።

“ከአጅፕ እስከ ደከር” ያለው መንገድ ብቻ ሳይሆን የኮሪደር ልማትም እያከናወን ነው። ኮሪደር ስንል ደግሞ ዝም ብሎ ኮሪደር አይደለም። የተመረጠ የጤና ኮሪደር እንጂ። የጤና ኮሪደሩ ሲባል የመንግሥትንም ሆነ የግል የጤና ተቋማትን የሚያገናኝ ነው። በዚህ ቦታ የጤና ኮሪደርን እንዲሆን የመረጥንበት ዋና ምክንያት እየተሠራ ባለው ልማት ዙሪያ በርካታ የጤና ተቋማት ስለሚገኙ እነሱን ለማገናኘት በማሰብ ነው።

ልማቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሕይወት ፋና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ሀይቤድ ድንገተኛ ማዕከል፣ የፌስቱላ ሆስፒታል፣ የክልላችን የጤና ቢሮ፣ የክልላችን “ሪጅናል ላብራቶሪ” እና ብዛት ያላቸው የግል የጤና ተቋማት መገኛ ነው። ፕሮጀክቱን የጤና ኮሪደር ያልነው አንደኛ አሁን ያሉትን የጤና ተቋማት አስበን ነው። ሁለተኛ ቀጣይ በዚህ አካባቢ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰጥ ከሆነ የሚሰጠው ፈቃድ በጤናው ዘርፍ ላይ ብቻ ነው ።

በአንድ አካባቢ የጤና ኮሪደሮችን መፍጠራችን አንደኛ ሕዝባችን ላይ እና ታች ሳይል፤ ሳይቸገር፤ የትራንስፖርት ወጭ ሳያወጣ አንድ አካባቢ ላይ የተሟላ የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ ስለሚያስችል ነው። ሁለተኛው በጤና ተቋማት መካከል ጤናማ የሆነ ውድድር እና ትብብር ለመፍጠር ታስቦ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሐረር ትልቁ አቅም ቱሪዝም ነው። በቱሪዝም ሐረር በዓለም ሀብትነት የተመዘገቡ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት ናት። በሚዳሰስ ቅርስ የጀጎል ግንብ አለን። በማይዳሰስ ደግሞ ሸዋልኢድ አለን። ከዚህ በተጨማሪ ሐረር ከፍተኛ የሆነ



የሜዲካል ቱሪዝም አላት።

እንደሚታወቀው በተለያዩ አጋጣሚዎች ሐረር በምስራቅ ኢትዮጵያ እንደማዕከል ስታገለግል የነበረች ከተማ ነች። በዚህም ለጤና አገልግሎት ከውስጥም ከውጭም በርካታ ሰዎች ይመጣሉ። አሁን ላይ ከሱማሌ ላንድ በርካታ ሰዎች ለሕክምና ወደ ሐረር ይመጣሉ። ስለዚህ የጤና ኮሪደር ልማቱ ለሜዲካል ቱሪዝሙ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት ከቻልን የሜዲካል ቱሪዝሙን እውን ማድረግ እንችላለን። ይህ የረጅም ጊዜ ራዕያችን ነው። አሁን እያደረግነው ያለው የጤና ኮሪደር ልማት ለዚህ እርሾ የሚሆን ነው ።

**አዲስ ዘመን ፡- የሐረር ከተማን የውሃ ችግር ለማቃለል የሚያግዙ ፕሮጀክቶች በቅርቡ ሲጠናቀቁ የማኅበረሰቡን የውሃ ችግር እንደሚቀረፍ ይታመናል። ይሁን እንጂ የመብራት መቆራረጥ ለዘርፉ ፈተና ሲሆን ይታያል። ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ምን ታቅዷል?**

**አቶ ኦርዲን፡-** የሐረር የውሃ ችግር ያደረ እና ለረጅም ጊዜ የቆየ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ይህን ችግር ለመፍታት በርካታ ጥረት ተደርጓል። ግን አሁንም መፍትሔ አላገኘም። አንዳንድ ጊዜ ችግሩ ሲባባስ ይታያል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መሻሻሎችን ያሳያል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሐረር ላይ የመጠጥ ውሃ ችግር አለ። ለዚህም ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ።

አንደኛው ውሃው ከድሬዳዋ አካባቢ ከ72 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚመጣ መሆኑ ነው። ከ72 ኪሎ ሜትር ላይ ተነስቶ ሐረር እስኪገባ ባለው ሂደት ከውሃው ምንጭ እና በሐረር ከተማ መካከል የሚገኙ ሌሎች ከተሞች ውሃ ይወስዳሉ። ለምሳሌ ደንገጎ፣ አዴሌ፣ ለሀሮሚያ እና ለአወዳይ ውሃ የሚወስዱት ለሐረር ከተማ የውሃ አገልግሎት እንዲውል በሚል በሐረሪ ክልል ሙሉ ወጭ ከተገነባው የውሃ መስመር ነው። ሐረር ውሃ የምታገኘው ይህን ሁሉ ቦታ ካዳረሰ በኋላ ነው።

አሁን በተጠቀሱት ከተሞች ያለው የሕዝብ ቁጥር ደግሞ እየጨመረ ነው። በመሆኑም በዚያ አካባቢ ጥቅም ላይ የሚውለው ውሀ እየጨመረ ነው። ይህ ደግሞ ሐረር መድረስ የነበረበትን ውሃ በእጅጉ ይቀንሰዋል። ለሐረር የውሀ እጥረት አንዱ ችግር ይህ ነው።

ሁለተኛው ችግር ደግሞ እጅግ ተደጋጋሚ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ነው። ከ72 ኪሎ ሜትር ወደ ሐረር የሚመጣው ውሃ ምንጩ ከጥልቅ ጉድጓድ የተገኘ ነው። የጉድጓዱ ጥልቀት አንድ ሺህ ሜትር ከፍታ ያለው ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል ሲቋረጥ ወደላይ በከፍተኛ ጉልበት ወደላይ ተገፍቶ የመጣው ውሃ እንደገና ተመልሶ ወደነበረበት ምንጭ ይመለሳል። ጉዳቱ ውሃው መመለስ ብቻ አይደለም። ውሃው ሲመለስ ብዙ ማሽኖችን ያበላሻል። እንደገና የተበላሸውን እቃ ለመተካት ደግሞ ሌላ ወጭ ይጠይቃል። በዚህ ሂደት በርካታ “ፓምፖች” ከጥቅም ውጭ ሆነዋል። በመሆኑም የኤሌክትሪክ መቆራረጥ እጅግ በጣም! ከባድ ችግር ሆኖ ይገኛል። በኃይል መቆራረጥ ሳቢያ ማኅበረሰቡ ከሁለት ሳምንት እስከ ሁለት ወር ድረስ ውሃ የማያገኝበት ጊዜ ይኖራል። በቃ! መብራት ከሌለ ውሃ የለም።

ሦስተኛው ችግር ደግሞ ውሃ የሚገኝባቸው ጉድጓዶች ጥልቅ በመሆናቸው ውሃው መቼ እንደሚያልቅ አለመታወቁ ነው። ለምሳሌ ሰባት ጉድጓድ ቢኖረን በአንድ ዓመት ሁለቱ ጉድጓድ ሊደርቅ ይችላል። የጉድጓድ ውሃ መቼ ያልቃል? የሚለውን በምንም መልኩ ማወቅ አይቻልም።

እንደመንግሥት ይህን ችግር ለመቅረፍ የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ እቅዶችን በማቀድ የተለያየ ተግባራትን እያከናወን ነው። በአጭር እና በመካከለኛ ጊዜ እቅድ ከተካተቱ ፕሮጀክቶች መካከል ኤረር በሚባለው አካባቢ ተጨማሪ ጥልቅ ጉድጓዶችን በመቆፈር የሐረርን የውሃ ችግር ለማቃለል ከሁለት ዓመታት በፊት የተጀመረ ፕሮጀክት አለ። ይህም የኤረር የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ይባላል።

የኤረር የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ስኬታማ ሆኖ ሲጠናቀቅ አሁን ካለው የውሃ ምርት በእጥፍ ይጨምራል። የኤረር የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አሁን ላይ ሥራው ተጠናቋል። ከግንቦት ወር 2016 ዓ.ም መጨረሻ በሰኔ ወር 2016 ዓ.ም መጀመሪያ ሥራ ይጀምራል። ይህም አሁን ያለውን የሐረር ከተማ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት በእጥፍ ጨምሯል። ይህ ለክልላችን መንግሥት እና ሕዝብ ትልቅ እፎይታ የሚፈጥር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ድሬዳዋ የሚገኙትን የውሃ ጉድጓዶችንም የማደስ እና ምርታማነቱን የመጨመር ሥራ እንሠራለን ።

የኤረር እና የድሬዳዋ ፕሮጀክቶች የሐረርን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጊዜያዊነት የሚቀርፍ እንጂ በዘላቂነት መፍትሔ የሚያመጣ አይደለም። በመሆኑም የሐረርን የመጠጥ ውሃ ችግር በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው አሁን በክልላችን በፌዴራል መንግሥት ኤረር ላይ በሚሠራው ግድብ ነው። ግድቡ የኤረር ግድብ የሚባል ሲሆን በርካታ ጥቅሞችን እንዲሰጥ ታቅዶ የሚሠራ ነው። ግድቡ ሲጠናቀቅ ለሚቀጥሉት ለ50 እና 60 ዓመታት የሐረርን የንጹሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ሙሉ በሙሉ መቅረፍ የሚያስችል ነው። ግድቡ ከመጠጥ ውሃ አገልግሎት በተጨማሪ ለመስኖ ሥራ እና ለመዝናኛነት የሚውል ነው።

የዚህ ፕሮጀክት ጥናት እና የዲዛይን ሥራ ተጠናቋል። በቀጣይ የግንባታ ሥራው ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን ፡- በግብርናው ዘርፍ ለአርሶ አደሩ የቀጥታ ትስስር በመፍጠር እና ሸማቹም ባልተጋነነ ዋጋ እንዲገዛ ለማድረግ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ኦርዲን ፡-** እንደ ሐረሪ ክልል ዋነኛው እምቅ ሀብታችን ቱሪዝም ነው። ይሁን እንጂ ገጠር ላይ በተለይም በግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው። በግብርና ውስጥ ደግሞ ለሌማት ትሩፋት ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው። የሌማት ትሩፋት ሥራው በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማም ተስፋ ሰጪ ሥራዎችን እየሠራን ነው፡፡

በክልላችን የወተት፣ የዶሮ፣ የእንቁላል እና የማር መንደሮች ብለን መንደሮችን እየመሠረትን ነው። ከሌማት ትሩፋት ጋር በተያያዘ የመንደር ምሥረታው ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። አሁን ላይ ወደ 21 የሚጠጉ የወተት፤ 14 የሚሆኑ የዶሮ መንደሮችን መሥርተናል። ይህን የመሰለ ሥራችንን በሚፈለገው ልክ ለማስፋፋት በርካታ ሥራዎች ይጠብቁናል።

ሌላው ከግብርና ጋር በተያያዘ እንደክልል በተጠናከረ ሁኔታ እያከናወናቸው ከሚገኙ ተግባራት መካከል በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን የተጀመረው “የግሪን ሌጋሲ” ሥራ ነው። ግሪን ሌጋሲ እንደ ሀገር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከ12 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ተክለናል። ለ2016 ክረምት ደግሞ 2 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኝ ለተከላ አዘጋጅተናል።

በዚህ ዓመት ከምንተክላቸው ችግኞች 70 በመቶው ለምግብነት የሚውሉ ዕፅዋትን ነው። ቀሪ 30 በመቶው ደግሞ የደን ዛፎች ናቸው። ስለዚህ በምግብ ራስን ለመቻል ከፍተኛ ፋይዳ አለው። የኑሮው ውድነቱን በማቃለል እና በሥራ እድል ፈጠራ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

እንደክልል የሌማት ትሩፋት ሥራዎችን ስንጀምር በኢኮኖሚ ደከም ያሉ ቦታዎችን እና የማኅበረሰብ ክፍሎችን ነው የመረጥነው። ይህ ደግሞ ድህነትን በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ነው።

ከግብርናው ጋር በተያዘ ምርታማነትን ከመጨመር አኳያ ጥረቶች ይደረጋሉ። ከተማው ላይ በብዛት ሕዝቡ ምን ምርት ይፈልጋል? የሚለውን በማጥናት ገጠር ላይ እያመረትን ነው። አርሶ አደሩ ምርቱን ካመረተ በኋላ በቀጥታ በሸማቹ እና በአምራቹ መካከል ምንም አካል ሳይገባ ከተማ ላይ ወስዶ ለሸማቹ እንዲያቀርብ እያደረግን ነው። በዚህም አሁን ላይ ቀድሞ የነበረውን የዋጋ ንረት በእጅጉ ማሻሻል ተችሏል። ነገር ግን አሁንም ይቀረናል።

**አዲስ ዘመን፡- አርሶአደሩ ያመረተውን ምርት በቀጥታ ለሸማቹ ለማቅረብ መንገዶች ወሳኝነት አላቸው። ከዚህ አንጻር በክልላችን አርሶአደሩን ከከተማው የሚያገናኙ የመንገዶች ግንባታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ኦርዲን፡-** እውነቱን ለመናገር ሐረር ላይ ብዙም የመንገድ ችግር የለም። ሐረሪ ክልል ላይ ቀበሌ ከቀበሌ በመንገዶች ተገናኝቷል በሚባልበት ደረጃ መንገዶች ተሠርተዋል። ከራሳችን ክልል አልፈን ከሌሎች ክልሎች ጋር ለመገናኘት መንገዶችን እየሠራን ነው። አሁን ላይ የአስፋልት ሥራ ገጠር ላይ ጀምረናል። በቀጣይ ደረጃውን የማሳደግ ሥራ እንሠራለን።

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት ሠርቶ አስረክቧል? ትውልድ ለሚቀርጹ መምህራን የመኖሪያ ቤት ሠርቶ መስጠቱ የክልሉን የትምህርት ጥራት ከማስጠበቅ አንጻር የሚኖረውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ኦርዲን፡-** የከተሞች አንዱ ትልቁ ጥያቄ መኖሪያ ቤት ችግር ነው። ከተሞች ባደጉ ቁጥር ሁልጊዜ ተጨማሪ የመኖሪያ ቤቶች ያስፈልጋሉ። ስለሆነም በከተሞች ላይ በመኖሪያ ቤት አማራጮች ላይ በጥናት የታገዙ ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ከዚህ አንጻር በሐረሪ ክልል የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል። ለነዋሪዎችም ተላልፈው ተሰጥተዋል። ነገር ግን እንደመምህራን አይነት ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የማኅበረሰባችን ክፍሎች አሉ። መምህራን ያለባቸውን ኃላፊነት እና የኑሮ ጫና ስትመለከት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የመምህርነት ሙያ ትልቅ ሙያ ነው፤ ሊከበር ይገባል። ምክንያቱም ያለመምህር ምንም የለም። ስለሆነም መምህር ላይ ሥራን መሥራት ያስፈልጋል። መምህራን ተቸግረው የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ አይቻልም።

በመሆኑም መምህራን ያለባቸውን የኑሮ ጫና ማቃለል ያስፈልጋል። ከዚህ በመነሳት ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት ገንብተን በዕጣ አስተላልፈናል። በክልሉ ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት ገንብተን ስንሰጥ አሁን ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ለመምህራን ቤት መስጠቱ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው። መምህራን ተረጋግተው የመማር ማስተማር ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እና ትውልድን የማነጽ ሥራቸውን እንዲሠሩ ያስችላቸዋል።

በሐረር ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት አለ። በቀጣይ ይህን ችግር ለመፍታት እንሠራለን። የውሃን ችግር ለመቅረፍ እንዳደረግነው የሐረርን ቤት ችግር ለመቅረፍ የአጭር እና የመካከለኛ እንዲሁም የረጅም ጊዜ እቅዶችን አቅድን እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- የሐረሪ ቤት አሠራር እና በውስጡ የሚከናወኑ ኩነቶች ለምሑራን እና ለሴቶች የሚሰጠው ክብር እንዲሁም ሌሎች የባሕሉ መገለጫዎቹ ኢትዮጵያውያን በመደበኛ ትምህርት ቢማሩት ትልቅ ጥቅም እንደሚያስገኝ ይነገራል። በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?**

**አቶ ኦርዲን፡-** የሐረሪ ቤት ራሱን የቻለ ብዙ ታሪክ ያለው ነው። ቤት ውስጥ ከገባህ በኋላ በቤቱ የሚከናወን እያንዳንዱ ነገር ትርጉም ያለው ነው። በሐረሪ ቤት የሚገኙ አምስት መቀመጫ መደቦች አሉ። መደቦች በደረጃ የተሠሩ ናቸው። እያንዳንዱ መደብ የየራሱ ትርጉም አለው። የተማረ ከላይ መደብ ይቀመጣል፣ ያልተማረ መሬት ላይ ይቀመጣል። የተማረ ከላይ መደብ ሲቀመጥ ያልተማረ ደግሞ ከታች ተቀምጦ ሻይ እንዲቀዳ ይደረጋል። ይህ የሚያሳየው ከድሮ ጀምሮ የሐረሪ ሕዝብ ለትምህርት የሚሰጠውን ትልቅ ዋጋ ነው።

በሐረሪ ባሕል ቤት እቃዎች አደራደር በምክንያት ነው። በመሆኑም በሐረሪዎች ቤት መብራት ቢጠፋ እንኳን የፈለከውን እቃ ሳትደናገር ታገኛለህ። የሐረሪ ሰዎች የትም ቦታ ቢሄዱ የሐረሪን ባሕል የሚያሳይ ቤት ይገነባሉ።

የሐረሪን ሕዝብ ባህል እና ታሪክ የሚዘክሩ ክንውኖች አስተማሪ እና ጠቃሚ በመሆናቸው ለትውልዱ በትምህርት ካሪኩለም አካቶ ማስተማር ያስፈልጋል። ይህን በቀጣይ የምናየው እና የምንሠራበት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ኦርዲን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

# ‹‹ሱፍ›› - የወንዶች ሙሉ ልብስ

ሰሚራ በርሀ



በተለምዶ ‹‹ሱፍ›› የምንለው የወንዶች ሙሉ ልብስ አይነት በወንዶች በስፋት እንደ ፕሮቶኮል ልብስ ተደርጎ ይወሰዳል፤ ለየት ላለ ፕሮግራምም ይመረጣል። ተማሪዎች በምረቃ ፕሮግራማቸው፣ በሠርግ ቀናቸው፣ በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎችም እንዲሁ ይህን የልብስ አይነት ምርጫቸው ያደርጉታል። ‹‹ሱፍ›› ወይም ሙሉ ልብስ የለበሰ ሰው በተለምዶ ‹‹ሙሽራ›› መስለሃል ተብሎ ሲገለጽም ይሰማል።

የኔነህ ጥላሁን ይባላል። በሽያጭ ሥራ ባለሙያነት የረጅም ዓመት ልምድ ያለው ሲሆን፣ በወንዶች ሙሉ ልብስ /የሱፍ ልብስ/ ሽያጭ ሥራ ውስጥ ስምንት ዓመታትን አስቆጥሯል። የሱፍ ልብስ በቀደመው ጊዜ ውስን የሆኑ ተጠቃሚዎች ነበሩት ሲል ገልጾ፣ ገበያው ላይ የነበረው የዲዛይን አማራጭም ጥቂት እንደነበር ይናገራል። አሁን ላይ ሱፍ ልብስን ምርጫቸው የሚያደርጉ ወንዶች ቁጥር በርከት እያለ መምጣቱንም ይጠቅሳል።

‹‹የበፊቱ የሱፍ አይነት ኮቱ ረጅም፣ ሰፊ እና ለመልበስም ከበድ የሚል ነበር፤ የሚለበሰውም ወቅት እየተጠበቀ ብቻ ነው›› የሚለው የኔነህ፣ አሁን ላይ ብዙ አማራጮች እንዳሉ ተናግሯል ።

እሱ እንዳለው፤ በገበያው ላይ በርከት ያለ የሱፍ ልብስ አይነት ይገኛል፤ ልብሱ በአብዛኛው ‹‹ቱ ፒስ እና ስሪ ፒስ›› ተብሎ ይለያል። ኮት ሰደርያ እና ሱሪ የያዘው ስሪ ፒስ ሲባል፤ ብዙዎች የሚመርጡት ደግሞ ኮት እና ሱሪ ብቻውን የያዘው ቱ ፒስ የሚባለውን ነው ።

በአሁኑ ወቅት እንደ ፋሽን ተደርጎ ብዙዎች ምርጫቸው የሚያደርጉት ከሰዎች የሰውነት ቅርጽ ጋር ተስማምቶ የተሠራ የሱፍ ልብስ ‹‹ስሊም ፊት›› የሚባለው መሆኑን ይገልጻል። ይህም የተስተካከለና ጠበብ ያለ ትከሻ እና እግሩም ጠባብ የሱፍ ስፌት አይነት ያለው ነው ይላል። የበፊቱ የሱፍ ስፌት ወጥ መሆኑን አስታውሶ፣ እግሩም ሆነ ትከሻው አካባቢ ያልተመጠነ ስፌት እንደነበረው ተናግሯል።

የኔነህ እንዳብራራው፤ የሱፍ ልብስ በተለያዩ የቀለም አማራጮች በገበያው ላይ ይገኛል። ጠቆር ያለ ሰማያዊ፣ ጥቁር ቀለም በብዛት የሚመረጡ የቀለም አይነቶች ናቸው።

‹‹አሁን ላይ ብዙ የቀለም ምርጫዎች አሉ፤ ሰዎችም የተለያዩ የቀለም አይነቶችን ይመርጣሉ›› ሲል የኔነህ ይገልጻል። ‹‹ኮሌክሽን›› የተሰኘ የሱፍ አይነትም እንዳለ ይገልጻል። እሱም የሱፉ ኮት እና የሱሪው ቀለም የተለያየ አይነት ሲሆን፣ ይህም የሱፍ ልብስን አዘውትረው ለሚለብሱ ሰዎች አልያም ሙሉ ሱፍ መልበስ ምርጫቸው ላልሆነ ሰዎች ከሚኖራቸው ሌላ ሱፍ ጋር አጣምረው እንዲለብሱ ያስችላቸዋል ።

በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሱፍ ልብስን ምርጫቸው የሚያደርጉ እና ከሱፍ ልብስ ውጪ የማይለብሱ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ሱፍ መልበስ ከዚያም ክራቫት ጨምሮ ማድረግ ጭንቀት የሚያሳድርባቸውም አይጠፉም። ለመጀመሪያ ጊዜ የሱፍ ልብስ ለመግዛት ወደ መሸጫ ቦታዎች የሚያመሩት ወጣቶች ከሆኑ ለምርቃ ሥነ-ሥርዓታቸው፣ ሲያገቡ አልያም የወዳጆቻቸው ሠርግ ላይ ሚዜ ሲሆኑ ነው።

ይህ የወንዶች የፕሮቶኮል ልብስ ተደርጎ የሚወሰደው ሱፍ በመላው ዓለም የሚታወቅ እና ተቀባይነትን ያገኘም ነው። ፈረንሳይ እና ጣሊያን በስፋት ይታወቁበታል። ወደ ሀገራችን የሚገቡ የሱፍ ልብሶችም ቱርክን ጨምሮ ሦስቱ ሀገራት በስፋት የሚታወቁባቸው ናቸው። ‹‹በሱፍ ልብስ ጣሊያንና ፈረንሳይ በጣም ስለሚታወቁ ዋጋቸውም ውድ የሚባል ነው። ከቱርክ የሚመጣው ግን ዲዛይኑም ጥሩ ነው ዋጋው ተመጣጣኝ ነው፡፡›› የሚለው የኔነህ፣ በሀገራችን አሁን ላይ የቱርክ የሱፍ ልብሶች በገበያው ላይ በስፋት እንደሚገኙ ይገልጻል ።

የሱፍ ልብስም እንዲሁ በእይታ በመውደድ ብቻ የሚለበስ አለመሆኑን የሚያነሳው የኔነህ፣ የትኛው የሱፍ ቀለም ከምን አይነት የቆዳ ቀለም ጋር፣ የትኛው ሱፍ ከየትኛው ሸሚዝ እና ከረቫት ጋር እንደሚሄድ ማወቅን ይጠይቃል ሲል ያብራራል።

ታዲያ ሱፍ ለመግዛት ያሰቡ ሰዎች እውቀት ኖሯቸው ይመጡ ይሆን ወይ ብለን ላቀረብንለት ጥያቄ ሲመልስም፤ ያለፉትን ሦስት ዓመታት ወንዶች በደንብ ስለ ሱፍ አጥንተውና የሚወዱትን አይነት መርጠው ሲመጡ ማስተዋሉን ተናግሯል። የሱፍ ልብስ ተስተካክሎ እና ተሰፍቶ ተዘጋጅቶ እንደሚሸጥ ጠቅሶ፣ የራሱ መጠን እንዳለውም ይገልጻል። ሰዎችም ሱፉን ሲገዙ ባላቸው የትከሻ ልክ የሚመጠን ፈልገው መሆኑን አመልክቶ፣ ከ44 ቁጥር ጀምሮ ግዙፍ እስከሚባለው እስከ 60 ቁጥር ድረስ ልብሱ ገበያ ላይ እንደሚገኝ፣ ልኬቱም ሙሉ ቁጥር ብቻ መሆኑን አስታውቋል።

እሱ እንዳብራራው፤ የሱፍ ልብስ ስፌት ችሎታ እና ጥንቃቄ ይፈልጋል፤ ወንዶች ምርጫቸው የሆነው ሱፍ ባይበቃቸው በጥንቃቄ የሚስተካከልበት ሁኔታ ይኖራል።

ቆንጆ ሱፍ የሚባል ቢኖርም፣ በሥራው የረጅም ዓመት ልምድን የያዘው የሽያጭ ባለሙያ ግን ሱፍ የማያምርበት ሰው እንዳለም ተናግሯል። እሱም ከትከሻ እስከ ወገብ እና ከወገብ በታች የሚኖረው የሰውነት ቅርጽ ያልተመጠነ ሲሆን ሱፉ የሚኖረውን ውበት እንደሚደብቀው አስተውሏል ።

የሱፍ ልብስ ስፌት አይነት ‹‹ሬጉላር ድሮፕ 7 ለቀቅ ያለ የስፌት አይነት እና ድሮፕ 6 የሰውነት ቅርጽን ተከትሎ የሚሄድ የስፌት አይነት ያለው ነው።›› ሲል አብራርቶ፣ የሱፍ ልብስ ብቻውን ውበት ያለው ቢሆንም ሸሚዝ፣ ከረባት እና ለየት ያሉ የጫማ አይነቶች ከሱፍ አለባበስ ጋር አብረው እንደሚሄዱ ገልጿል። ይህም ምርጫ ጥንቃቄ እንደሚሻ የኔነህ ያነሳል ፡፡

እሱ እንዳስታወቀው፤ ሱፍ አሁን ላይ ቀለል ባለ መንገድ ሊዘጋጅም ይችላል፤ ለየት ላለ ፕሮግራም የሚለበሱ የሱፍ አይነቶችም አሉ። ልክ እንደ እንስቶች ቬሎ ለሠርግ ብቻ ተብሎ የተመረጠ የሱፍ አይነትም አለ። በመሆኑም ሱፍ ለመግዛት የወሰኑ ወንዶች የሱፉን ጥራት፣ ከእነርሱ ቀለም፣ ተክለ ሰውነት ጋር አብሮ የሚሄደውን ማየት ይገባቸዋል። አንድ ሱፍ የሚሸጥበት ዋጋ እንደሚመጣበት ሀገር፣ የጨርቅ አይነት ይለያያል።

የሕግ ባለሙያዎች፣ የባንክ ሠራተኞች፣ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በቢሮ ውስጥ የሚያሳልፉ የቢዝነስ ሰዎች ሱፍን ያዘወትራሉ።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ወደኋላ እንዳንመለስ?

ሚዛን ስሜ

ባለፉት ጥቂት አስርተ ዓመታት ከፍተኛ እመርታ ከታየባቸው ነገሮች መሐከል አንዱ የሴቶች መብት ጉዳይ ነው። ሴቶችን ልጅ ከመውለድ እና ምግብ ከማብሰል ጋር ብቻ አስተሳስሮ የኖረውን ዘልማዳዊ አስተሳሰብ አስተካክሎ ሴት ልጅ ቦታዋ ማዕድቤት እና መኝታ ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤት እና ቢሮም ውስጥ እንደሆነ ለማስተማር ብዙ ተጥሯል። በርካታ ስኬትም ተገኝቷል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ተደርጓል። በሥራው ዘርፍም ለወትሮው ለሴቶች አይደፈሩም ተብለው የሚገመቱ የሥራ መስኮች ሴቶች በከፍተኛ ቁጥር የሚሳተፉባቸው እየሆኑ መጥተዋል፡፡

በምክር ቤቶች በከፍተኛ ቁጥር እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ካቢኔም እስከ 50 በመቶ በሚደርስ መጠን ሴቶች ድርሻ እንዲይዙ መደረጉ የዚህ እመርታ መገለጫ ነበር። የጠለፋ ጋብቻን፣ ግርዛትን እና መሰል ጎጂ ባሕልን እንዲቀንስ ማድረግ መቻሉም ከብዙዎቹ ስኬቶች መሐከል ተጠቃሽ ነበር፡፡

በቅርብ ጊዜያት ግን እነዚህን ስኬቶች ሁሉ አደጋ ውስጥ የሚከት ዝንባሌ እየታየ ነው። የት ከተባለም በማኅበራዊ ሚዲያ ነው። በማኅበራዊ ሚዲያው የሴቶች መብት የማስከበር ትግሉን የሚጋፉ ትርክቶች እየተበራከቱ ይመስላል። ሴትን ወደኋላ የሚመልሱ፣ አባታዊ (patriarchal) ሥርዓትን መመለስ የሚፈልጉ አስተሳሰቦች በየቦታው ብቅ እያሉ ነው። አንዳንዶቹ ክርክሮች የፌሚኒዝምን እንቅስቃሴ በመቃወም የሚደረጉ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ባሕላችንን እናስከብራለንም የሚሉ ናቸው።

እርግጥ ነው ባሕላችን መከበር አለበት። ቤተሰብን አስኳል ያደረገ ማኅበራዊ መዋቅራችን ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ከምዕራባውያን እሴት የሚቀዱ እና ኢትዮጵያዊውን ማኅበራዊ አኗኗር የሚጋፉ ንቅናቄዎች አይጠቅሙም። ይህ ማለት ግን ፌሚኒዝም መጥፎ ነው ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፌሚኒዝም (አለ የሚባል ከሆነ እንኳን) አደገኛ ነው ማለት አይደለም። ወደኋላ ተንሸራትተን ሴትን ልጅ ወደ ማድቤት ባለቤት እና ወደ መኝታ ቤት ጌጥነት እንመልሳለን ማለትም አይደለም። በቅርብ ጊዜ የሚታዩ የሶሻል ሚዲያ ክርክሮች ግን መንፈሳቸው ወደዚያ የተቃረቡ ናቸው፡፡

ፌሚኒዝምን አለቅጥ ማራከስ፥ የወንድ ልጅን የበላይነት የሚሰብኩ ቅስቀሳዎችን ማብዛት (ሲግማ ወንድ እና መሰል አይነት የሰሞኑ ፌስቡክ እና የቲክቶክ ዘመቻ)፣ ሴት ልጅ እንዲህ ስትሆንና እንደዚያ ስትሆን ብቻ ነው የሚያምርባት የሚል ፍረጃ ፣ መብታቸውን የሚጠይቁ ሴቶችን በአካላዊ ገጽታቸው ማራከስ፣ በየቦታው የሚታይ የሴት ልጅ እገታ እና መሰል እንቅስቃሴዎች ጤናማ አይደሉም፣ ውጤታቸውም የሚያምር እንደማይሆን እርግጥ ነው። ይሄ ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚታይ ጤናማ የማይመስል ውይይት ለጊዜው ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ብቻ ስለሚታይ ተራ የፌስቡክ ወሬ እና የቲክቶክ ማድመቂያ ቢመስልም በጊዜ ሂደት ግን ወደ መደበኛው ሚዲያም ሆነ ወደ እለታዊ ኑሮ የሚሻገር ችግር መሆኑ አይቀርም። በእርግጥ እስካሁን በሴቶች ጉዳይ ከመንግሥት በኩል አዲስ የተያዘ አሉታዊ አቋም ባይኖርም ነገር ግን መንግሥት በሴቶች መብት ዙሪያ አሁንም አቋሙ ጠንካራ እንደሆነ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡

**ሴትን ወደኋላ የሚመልሱ፣ አባታዊ (patriarchal) ሥርዓትን መመለስ የሚፈልጉ አስተሳሰቦች በየቦታው ብቅ እያሉ ነው። አንዳንዶቹ ክርክሮች የፌሚኒዝምን እንቅስቃሴ በመቃወም የሚደረጉ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ባሕላችንን እናስከብራለም የሚሉ ናቸው**

እዚህ ጋር የሚነሳ ጥያቄ ይኖራል። ጥያቄውም መንግሥት የሰዎችን ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት እንዲያግድ ነው ወይ ጥያቄው? ሊባል ይችላል፣ መልሱም አይደለም የሚል ነው። የሴቶች መብት መከበር ያለበትን ያህል ሀሳብን የመግለጽ መብትም ሊከበር ይገባል። አንድ ሰው ሴት ልጅ ድርሻዋ ሚስት እና እናት መሆን ብቻ ነው ብሎ ሊያስብም ይችላል። ለምን አሰብክም ሆነ ለምን ተናገርክ ሊባል አይቻልም። ነገር ግን እንዲህ አይነት ሀሳብ ያለው ሰው ወይም ቡድን በሚኖርበት ጊዜ መንግሥት ወገንተኝነቱ ለማን እንደሆነ በግልጽ ማሳየት አለበት። አሜሪካም ሆነ አውሮፓ ውስጥ እንዲህ አይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች አሉ። ስለ ሀሳባቸው የደረሰባቸው በደል የለም። ነገር ግን መንግሥት በንግግርም ይሁን በተግባር በሚያወጣቸው ሕጎች እና ፖሊሲዎች ወገንተኝነቱ ለሴቶች እኩልነት ነው። እዚህም መሆን ያለበት ይሄው ነው፡፡

መንግሥት ይሄን ማድረግ ያለበትም ያለው ብቸኛ አማራጭ ይህ ስለሆነ ነው። ካሁን በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችን ወዳለፈው ዘመን የወንድሞቻቸው የበታች እና የራሳቸው ፍላጎት የሌላቸው የባሎቻቸው ንብረት ማድረግ አይቻልም። ይህ መሆን የማይችልበት ብዙ ምክንያትም አለ። ስለዚህም የማይሆነውን ነገር ለመመለስ መታገል የለብንም። ይልቁንም ከምዕራቡም ይሁን ከየትም ያልተቀዳ ለኢትዮጵያዊት ሴት የሚገባ እና የሚመጥን ሥርዓት ለመፍጠር መሥራት አለብን። በማኅበራዊ ሚዲያ ስለሴቶች የሚሠሩ ይዘቶችን የሚያዘጋጁ ሰዎች ያለንበት ዘመን 21ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ማስታወስ እና ወዳልኖሩበት ዘመን እያዩ መናፈቅ መተው አለባቸው።

# ስፖርት





## ኮከቦች የዘነጉት የሯጮች ምድር

**ብርሃን ፈይሳ**

በጎረቤት ሃገር ኬንያዋ ኤልዶሬት ከተማ 17 ኪሎ ሜትር ላይ የምትገኘውና ኢትን የተባለው ስፍራ ከኢትዮጵያዊዋ በቆጂ ጋር የሚመሳሰል ነው። «የቻምፒዮናዎች ቤት» በሚል ቅጽል የሚታወቀው ይህ ስፍራ ለአትሌቲክስ ስፖርት የተመቸ የአየር ንብረት እና መልክዓ ምድር ያለው ሲሆን፤ በርካታ ውጤታማ አትሌቶችንም አፍርቷል። ከግዙፍ የስፖርት ትጥቅ አምራች ድርጅቶች መካከል አንዱ የሆነው አዲዳስን ጨምሮ በርካታ የሥልጠና ማዕከላትና ካምፖች የተገነቡበት እንዲሁም ለስፖርቱ የተመቹ መሠረተ ልማት የተሟላበት አካባቢ ነው። ይህም ከሌላ ሃገራት ለልምምድ ወደስፍራው የሚያቀኑ አትሌቶችን ጨምሮ ለበርካቶች ሳቢ እንዲሆን አስችሎታል። በአፍሪካ እምብዛም ያልተስፋፋው የስፖርት ቱሪዝም ሃሳብ በእርግጥም እየተሠራበት ያለ የኬንያውያን መመኪያ የሆነ ስፍራ ነው።

በአርሲ ዞን መገኛዋን ያደረገችው የኢትዮጵያዊዋ በቆጂም ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ፋጡማ ሮባ፣ እጅጋየሁ ዲባባ፣ ገንዘቤ ዲባባ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ታሪኩ በቀለ፣ ቲኪ ገላና፣ መስታወት ቱፋ፣ ትዕግስት ቱፋ፣ ለሜቻ ግርማ፣... የመሳሰሉት የኦሊምፒክ፣ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና እንዲሁም ሌሎች የአትሌቲክስ ሻምፒዮን የሆኑ አትሌቶች ወጥተውባታል። የቦታ አቀማመጡ፣ የአየር ሁኔታው፣ ከዓመት ዓመት የሚዘልቀው የአካባቢው ልምላሜ፣ ሩጫን ባሕሉ ያደረገ የማኅበረሰቡ አኗኗር፣... ዛሬም ድረስ እየተተካኩ ላሉ አትሌቶች መፈጠር ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ ካገኘቻቸው 58 ሜዳሊያዎች መካከል 18 የሚሆኑት ሜዳሊያዎች(10የወርቅ፣ 3 የብር እና 5 የነሐስ) ከዚህ ስፍራ በተገኙ አትሌቶች የተሰበሰቡ በመሆናቸውም «የሯጮቹ ምድር» የሚል ቅጽልን አግኝቷል።

በተፈጥሮ ሃብት የታደለውና የአትሌቶች ምንጭ ከሆነው ከዚህ ስፍራ በርካታ የውጪ ዜጋ አትሌቶች ከበረከቱ ሊካፈሉ የሚመኙት፤ የአትሌቲክስ ወዳጆችም ሊጎበኙት የሚሹት ቢሆንም መሠረተ ልማት ማግኘት ያልተሟላለት በመሆኑ ምቹ አይደለም። ታዳጊ አትሌቶችም በተፈጥሮው ታግዘው በጥረታቸው ያለሙበት ለመድረስ ከመፍጨርጨር ባለፈ፤ መም ለመጠቀም ወደሌላ ስፍራ መጓዝ ይጠበቅባቸዋል። ከብቸኛው የበቆጂ አትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከል ባለፈ፤ አትሌቶችን ታሳቢ ተደርገው የተገነቡ የኮሮኮንች መሮጫዎችም ሆነ የልምምድ ስፍራዎች የሉትም። ስታዲየሙም ከደረጃ በታች ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በዓመት አንዴ ከሚያካሂደው ውድድር ባለፈ ስፍራው የሚነሳበት አጋጣሚም የለም። ይገነባል የተባለው የበቆጂ ሙዚየምም ከሃሳብ ወርዶ እውን ሳይሆን ዓመታት ተቆጥረዋል። ለጎብኚዎች የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ የማረፊያ ስፍራዎችና ሌሎች አገልግሎቶችም እጅግ ደካማ የሚባሉ ናቸው።

ይህ ሁኔታ ከጎረቤት ሃገር የኬንያዋ ኤልዶሬት ኢትን ጋር በቆጂን ለማነጻጸር አዳጋች ያደርገዋል። ለችግሩ በምክንያትነት የባለሃብቶች ተሳትፎ አናሳነት ቢነሳም ከስኬት ማማ ላይ የሚገኙ አንጋፋ አትሌቶች ውለታቸውን አለመመለስ ግን ጉልህ ድርሻ የሚሰጠው ነው። የበቆጂ ከተማ ከንቲባ ብርሃኔ ነገሰ፤ ለአትሌቲክስ ስፖርት ምቹ የሆነውን ስፍራ በመላው ዓለም የታወቀ የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል ማድረግ ቢቻልም በመንግሥት ብቻ የሚከናወን ሥራ አለመሆኑን ይጠቁማሉ። በመሆኑም የስፍራው ተወላጅ የሆኑ አትሌቶች ላሉበት ደረጃ



**በርካታ ወርቅማና ታሪካዊ ኦሊምፒያንን ያፈራችው በቆጂ፣**

የበቁበትን የትውልድ ስፍራ ዞር ብለው ሊመለከቱ ይገባል። «ያኔ እነደራርቱ የሮጡበት ሜዳ አሁንም እንዳለ ነው ያለው» የሚሉት ከንቲባዋ በየጊዜው በተሻለ ይሠራበታል ተብሎ ቃል ቢገባም በመንግሥት አቅም ብቻ ማሳካት አልተቻለም። ከበቆጂ የወጡ ትልልቅ አትሌቶች ውድድሩን ተከትሎም ግብዣ ሲደረግላቸውም ባልታወቀ ምክንያት አይገኙም። ነገር ግን በቀጣይ ሊሳተፉበት የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች የሚመቻች ሲሆን፤ ባለሃብቶችም እምቅ በሆነ የቱሪዝም ሃብት በካበተው በዚህ ስፍራ ላይ በመሥራት ሃገርን ማሳደግ እንደሚገባቸውም አስገንዝበዋል።

ከበቆጂ የወጡ አትሌቶች የስፖርት ቱሪዝምን በማበረታታት ረገድ በተለይ ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚገልጹት ደግሞ የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ናቸው። ያፈራቸው ምድርና ያሳደጋቸው ማኅበረሰብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ፣ ቦታውን ማሳወቅና የቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ውድድሩ በሚካሄድበት ወቅት ተሳታፊ እንዲሆኑ ለእነዚህ አትሌቶች ግብዣ ቢቀርብላቸውም ሊገኙ አልቻሉም። ሆቴሎችን በመገንባትም ሆነ በሌሎች ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ረገድ ከአትሌቶች ባለፈ ከባለሃብቶች፣ መንግሥት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት በርካታ ሥራዎች እንደሚጠበቁም አሳስበዋል።


# የሐራጅ ማስታወቂያ

አማራ ባንክ አ.ማ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የመኖሪያ ቤቶች እና ጋራዥ በግልጽ የሐራጅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው ስም | የንብረት አስያዥ ስም | አበዳሪው ቅርንጫፍ | የንብረቱ ኣድራሻ | | | የቦታው ስፋት | የቦታው መለያ ቁ. | የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቁጥር | የንብረቱ ዓይነት | የጨረታ መነሻ ዋጋ | ጨረታው የሚከናወንበት | | ጨረታው ለምን ያህል ጊዜ ወጥቷል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | ቀን | ሰዓት | |
| 1 | ከኛ ወዲያ ላቀው ሀብተመስዋል | ከኛ ወዲያ ላቀው ሀብተመስዋል | ሴቻ | አርባ ምንጭ | ሲቀላ | ድል ፋና | 200 ካሬ | ASDR-481 | ል/ቀ/ማ/ ቤታዊ/884/15 | የመኖሪያ ቤት | 5,173,219.03 | ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ.ም | ከ3፡00- 6፡00 ሰዓት | ለሁለተኛ ጊዜ |
| 2 | ደሳለኝ ኃ/ሚካኤ ወ/ጊዮርጊስ | ደሳለኝ ኃ/ሚካኤ ወ/ጊዮርጊስ | አዳማ አባገዳ | ሞጆ ከተማ | ወረዳ 2 | 01 ቀበሌ | 157 ካሬ | | 221/07 | የመኖሪያ ቤት | 5,119,619.76 | ሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም | ከ3፡00- 6፡00 ሰዓት | ለመጀመሪያ ጊዜ |
| 3 | ደሳለኝ ኃ/ሚካኤ ወ/ጊዮርጊስ | ዮርዳኖስ ደለለኝ ሙሉነህ | አዳማ አባገዳ | ሞጆ ከተማ | ወረዳ 2 | 01 ቀበሌ | 247.49 ካሬ | | 861/2011 | የመኖሪያ ቤት | 7,427,649.23 | ሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም | ከ3፡00- 6፡00 ሰዓት | ለመጀመሪያ ጊዜ |
| 4 | አበራ ካሰ ገ/ዮሃንስ | ካሳ ገ/ዮሃንስ ሽብሩ | ባህር ዳር | ባህር ዳር ከተማ | ዳግማዊ ምኒሊክ | 14 ቀበሌ | 2000 ካሬ | | 30360/06 | ጋራዥ | 8,752,992.31 | ሐምሌ 7 ቀን 2016 ዓ.ም | ከ3፡00- 6፡00 ሰዓት | ለመጀመሪያ ጊዜ |

**ማሳሰቢያ፤**

1. ተጫራቾች የጨረታ መነሻ ዋጋ 1/4 ወይም ሃያ አምስት በመቶ (25%) በባንክ የተረጋገጠ የክፊያ ሰነድ (C.P.O) በአማራ ባንክ አ.ማ ስም በማሰራት ቀርበው መመዝገብና በጨረታው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።
2.ጨረታው አሸናፊ ቀሪውን ገንዘብ በ15 (አሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ አጠናቆ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ባይከፍል ግን የሐራጁ ውጤት ተሰርዞ ያስያዘው ገንዘብ አይመለስለትም፣ ለባንኩ ገቢ ይሆናል፡፡ ላላሸነፉት ተጫራቾች ግን ያስያዙት ገንዘብ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል።
3. የጨረታው አሸናፊ ባሸነፈበት ዋጋ ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ይከፍላል፡፡
4. ንብረቱ በገዥው ስም እንዲዞር ባንኩ ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል ደብዳቤ ይጽፋል፡፡
5. ጨረታው የሚካሄደው በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተገለጸውን በተመለከተ አርባ ምንጭ ከተማ በሚገኘው የባንኩ ሴቻ ቅርንጫፍ፤ በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተገለጸውን በተመለከተ በሞጆ ከተማ በሚገኘው የባንኩ ሞጆ ቅርንጫፍ፤በተራ ቁጥር 4 ላይ የተገለጸውን በተመለከተ በባህር ዳር ከተማ በሚገኘው የባንኩ ባህር ዳር ቅርንጫፍ ውስጥ ነው፡፡
6. የተጫራቾች የምዝገባ ሰዓት በዕለቱ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 5፡00 ሰዓት ብቻ ነው፡፡
7. የጨረታው ጊዜ እስከ 6፡00 ሠዓት ቢሆንም ጥሪ እየተደረገ ከሆነ ጨረታው በሠዓት አይገደብም፡፡
8. ለሐራጅ የቀረበውን ንብረት ለመጎብኘት የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች የጉብኝት ፕሮግራም ከሕግ አገልግሎት መምሪያ ጋር አስቀድሞ ቀጠሮ በማስያዝ መጎብኘት ይችላል፡፡
9. ተበዳሪው በጨረታው ቀንና ሰዓት በቦታው ላይ መገኘት ይችላል፡፡ ነገር ግን ተበዳሪው ባይገኝም ጨረታው በሌለበት ይካሄዳል። ጨረታው ላይ መገኘት የሚችሉት ተጫራቾች ወይም የተጫራቾች ሕጋዊ ተወካዮች ብቻ ናቸው፡፡
10. በንብረቱ ላይ ከመንግስት የሚፈለጉ ግብሮችን/ታክስ፤ የስም ማዛወሪያ እና ሌሎች ማናቸውም አይነት ወጪዎችን የሊዝ ክፍያን ጨምሮ የጨረታ አሸናፊው ይሸፍናል፡፡
11, ባንኩ የተሻለ መንገድ ካገኘ በጨረታው አይገደድም፡፡
12. ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0115584001 መደወል ይችላሉ፡፡

**አማራ ባንክ አ.ማ.**